# የኢትዮጵያ የ2010/2011 የሰብዓዊ መብቶች ሪፖርት

## አጭር ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ፌዴራል ሪፑብሊክ ናት። ገዢው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) በብሔር ላይ በተመሰረቱ አራት ፓርቲዎች የተቋቋመ ግንባር ሲሆን፣ ይህ ድርጅት መንግሥትን ይቆጣጠራል። በ2015 (2007 ዓ/ም) በተካሄደው አጠቃላይ ምርጫ ኢሕአዴግ እና አጋር ድርጅቶች፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ) 547 መቀመጫዎችን በሙሉ አሸንፈው ግንባሩ ለአምስተኛ ተከታታይ ጊዜ በሥልጣን ለመቆየት የሚያስችለውን ሥልጣን አግኝቷል። ፌብርዋሪ 14 (የካቲት 7)፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ትዕግስቱ እየተሟጠጠ የመጣውን የወጣቱን ክፍል ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲቻል የፖለቲካ ማሻሻያዎችን ለማፋጠን በሚል ምክንያት ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እንደሚለቁ አስታወቁ። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በሄደው ግርግር እና የፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት በፌብርዋሪ 15 (የካቲት 8) መንግሥት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አወጀ። በዚህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመከላከያ ሚኒስትር የሚመራ የዕዝ ጣቢያ የተቋቋመ ሲሆን፣ ይህ ኮማንድ ፖስት በሕገ መንግሥት የተከበሩ ሰብዓዊ መብቶችን እንኳን ለመጣስ የሚያስችል ሥልጣን ተሰጠው። በዚህም መልኩ ግለሰቦችን የማሰር፣ ሃሳብን የመግለጽ መብትን እና እንቅስቃሴን የመገደብ ሰፊ ሥልጣን አገኘ። በኤፕሪል 2 (መጋቢት 24) ቀን፣ ፓርላማው ሰፊ የሪፎርም (የማሻሻያ) ሥራዎች እንዲያከናውኑ አቢይ አሕመድ አሊን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሾማቸው።

አንዳንድ ጊዜያት የሲቪል ባለሥልጣናት የክልል የጸጥታ ኃይሎችን ለመቆጣጠር ሳይችሉ መቅረታቸው ተዘግቧል። የገጠር የአካባቢ ፖሊስ እና የሚሊ አባላት በራሳቸው ሲንቀሳቀሱ እና ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እርምጃ ሲወስዱ ነበር። የሕግ የበላይነትን በይበልጥ የማክበር አዝማሚያ መታየት የጀመረው በአቢይ አሕመድ አስተዳደር ነው።

አቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ አዎንታዊ ለውጦች መምጣት ጀመሩ። መንግሥታቸው ቀደም ሲል በአገር ክህደት የተከሰሱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ከወንጀል ፍረጃ ነጻ እንዲሆኑ አደረገ፤ ተቃዋሚ የፖለቲካ መሪዎች ወደ አገሪቱ ተመልሰው እንዲንቀሳቀሱ ፣ ሰላማዊ ሰልፎችን ማድረግ እንደሚቻል ተፈቀደ፣ ከተጽዕኖ ነጻ የሆኑ አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሚዲያ ተቋማት እንዲመሰረቱ ተደረገ፤ ተጨማሪ በሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞች ከእስር የሚፈቱባቸውን እርምጃዎች ወሰደ እንዲሁም አፋኝ ሕጎች

እንዲከለሱ ተደረገ። በጁን 5 ቀን (ግንቦት 28) ፓርላማው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እንዲነሳ ውሳኔ ሰጠ።

የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተብለው የሚጠቀሱት፡- ሰዎች ከሕግ ውጪ እና በዘፈቀደ በጸጥታ ኃይሎች መገደላቸው እና ዜጎች እርስ በእርስ መገዳደላቸው፤ አንዳንድ ሰዎች በመንግሥት ኃይሎች እንዲሰወሩ መደረጋቸው፣ ሰቆቃ መፈጸም ወይም ማሰቃየት፤ እጅግ አሰቃቂ እና ለሕይወት አስጊ የሆኑ የእስር ቤት ሁኔታዎች፤ የጸጥታ ኃይሎች በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል እና በእስር ማቆየት፤ የፖለቲካ እስረኞች መኖር ፤ በግላዊ መብት ላይ ጣልቃ መግባት፤ ሳንሱር እና ድረ ገጾችን መዝጋት/ማገድ፤ በሰላማዊ ስብሰባ እና የመደራጀት መብት፣ ለምሳሌ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ላይ እጅግ የበዛ ቁጥጥር የሚያደርጉ ሕግጋት መኖራቸው፤ እንዲሁም በእንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ገደብ ማድረግ፤ በሴቶች እና ሕጻናት ላይ የኃይል ድርጊት መፈጸም፣ ይህም በተወሰነ ደረጃ በመንግሥት ዳተኝነት ምክንያት መሆኑ፤ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነትን ወንጀል ማድረግ እንዲሁም የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ እጅግ ከባሱት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ከስፋት እና ጥልቀት አንጻር በአቢይ አስተዳደር በከፍተኛ ደረጃ የቀነሱ ከመሆናቸው ባሻገር አንዳንድ ሁኔታዎች በዓመቱ መጨረሻ ችግር መሆናቸው አብቅቶለታል።

መንግሥት አልፎ አልፎ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በፈጸሙ ባለሥልጣናት ላይ እርምጃ ሳይወስድ ቀርቷል፤ ይህም መሆኑ ጥፋተኞች ሳይጠየቁ እንዲታለፉ ሆኗል። በጸጥታ ኃይሎች እና በሕዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመቀየር እና የተሻለ ተጠያቂነትን ለማስፈን የአቢይ አስተዳደር አዎንታዊ እርምጃዎች ወስዷል። በነሐሴ ወር የፌደራል መንግሥቱ በሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት የቀድሞ የሶማሌ ክልል ፕሬዚደንት የነበሩትን አብዲ መሐሙድ ዑመርን በቁጥጥር ስር አዋለ። ጁን 18 (ሰኔ 11) ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለመላው የአገሪቱ ሕዝቦች ንግግር በማድረግ ለአስርተ ዓመታት ለተፈጸሙ ስህተቶች እና ከሽብር ድርጊት ጋር ሊመሳሰሉ ለሚችሉ ጥቃቶች መንግሥትን በመወከል ይቅርታ ጠየቁ።

## ክፍል 1፡- የሰውን ልጅ በሰውነቱ ማክበር፣ ከዚህ ከሚከተሉት እና ከሌሎችም ነጻ መሆን

## ሀ. በዘፈቀደ ሕይወትን ከማጣት ፣ እንዲሁም ሌሎች ከሕገ ውጪ እና በፖለቲካ ምክንያት ከሚፈጸሙ ግድያዎች

መንግሥት እና ወኪሎቹ የዘፈቀደ እና ሕገወጥ ግድያዎችን ስለመፈጸማቸው በርካታ ሪፖርቶች ነበሩ። የጸጥታ ኃይሎች በሰላማዊ ዜጎች ላይ ከሚፈለገው በላይ ኃይል ተጠቅመዋል።

ጁላይ 31 (ሐምሌ 24) የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (HRCO) የተሰኘ ገለልተኛ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት (NGO) በኦሮሚያ እና ሶማሌ ክልሎች ሰባት ዞኖች በሚገኙ 26 ወረዳዎች በሰነድ ተደግፎ በተካሄደ የመስክ ምርመራ ከጃንዋሪ 2017 (ከጥር 2009) እስከ ጃንዋሪ 2018 (ጥር 2010) ባለው ጊዜ የፌዴራል እና የክልል የጸጥታ ኃይሎች እና የአካባቢ አመፀኛ ወጣቶች 733 ዜጎች ገድለዋል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጆ በነበረበት ጊዜ በኤፕሪል 8 (መጋቢት 30)፣ በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን የቆቦ ከተማ ወታደራዊ ባለሥልጣን የሆነ ሰው የአንድ ልጅ እናት እና የሦስት ወር ነፍሰጡር የነበረች አያንቱ መሐመድ የተባለችን የ20 ዓመት ሴት ጠልፎ ከወሰዳት በኋላ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶባት ተኩሶ ገድሏታል የሚል ሪፖርት ቀርቧል። በአካባቢ ዜና ማሰራጫ በቀረበ ሪፖርት መሠረት፣ የአያንቱ ሬሳ ተጥሎ በቀጣዩ ቀን ተገኝቷል። የአካባቢው ፖሊስ እንደገለጸው ተጠርጣሪውን ወታደራዊ ሹም ትጥቁን አስፈትተውት ታስሯል።

ኦገስት 4 ቀን (ሐምሌ 28)፣ በሶማሌ ክልል ዋና ከተማ በጅግጅጋ እና በአጎራባች ከተሞች በተከሰተ ብጥብጥ ምክንያት ቢያንስ 30 የሚደርሱ ሰዎች ተገድለዋል። ከዚያ በኋላ በተከሰቱ ተደጋጋሚ ረብሻዎች በድሬዳዋ አንዲትን ሴት እና አራት ልጆቿን ጨምሮ 14 ሰዎች ሕይወታቸውን ማጣታቸውን የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ በኦገስት 7 (ነሐሴ 1) ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ ተገልጾዋል። ኦገስት 12 (ነሐሴ 6) ቀን በከፍተኛ ደረጃ የታጠቁ የሶማሌ ልዩ ኃይል አባላት (አንዳንድ ጊዜ ልዩ እየተባሉ የሚጠሩ) በኦሮሚያ ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ማዩ ሙሉቄ በተባለ ወረዳ በሚኖሩ ነዋሪዎች ላይ ጥቃት አድርሰው በዚህ ሳቢያ 40 ሰዎች ሲገደሉ 40 ሰዎች ደግሞ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። የኦሮሚያ ክልል መንግሥት አፈ-ጉባዔ ለአካባቢ ዜና ማሰራጫ እንደገለጸው ጥቃት ፈጻሚዎቹ ትዕዛዝ የተቀበሉት የፌደራል መንግሥቱን ከሚቃወሙ ግለሰቦች ነው ብለዋል።

## ለ. መሰወር

መንግሥት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ጨምሮ ግለሰቦችን ለተወሰነ ግዜ በቁጥጥር ስር አውሎ ሰውሯቸው ነበር። በሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ጁላይ 31 (ሐምሌ 24) ቀን በወጣ ሪፖርት መሠረት፣ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ነዋሪ የሆኑ

ዘጠኝ አዋቂ ሰዎች በሶማሌ ክልል ልዩ ኃይል በደረሰባቸው ጥቃት ምክንያት ከአካባቢው ተሰውረዋል። የልዩ ታጣቂዎች ሰዎቹን የጠለፏቸው ከመንገድ ላይ ወይም ከየቤታቸው ነበር፡ ፡ በእስር ቤቶች አስተዳደር ችግር ምክንያት የቤተሰቦቻቸው አባላት እንደጠፉ ሪፖርት ያሰወቁ ሰዎች ቤተሰቦቻቸውን እስር ቤት/የቀጠሮ እስረኛ ማቆያ ሊያገኟቸው ሳይችሉ ቀርተዋል።

## ሐ. ማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት

ሕገ መንግሥቱ እንዲህ ያሉትን ተግባራት የሚከለክል እንኳን ቢሆን የጸጥታ ኃይሎች ታሳሪዎች ላይ ሰቆቃ አለበለዚያ ጥቃት ይፈጽሙባቸው እንደነበር ሪፖርቶች ቀርበዋል።

በኦክቶበር 2017 (2010) የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (EHRC) የተባለ መንግሥታዊ የሰብዓዊ መብቶች መሥሪያ ቤት ከታሳሪዎች በቀረበለት ይፋዊ አቤቱታዎች ላይ ተመስርቶ ባካሄደው ምርመራ የእስር ቤት ኃላፊዎች እና የፖሊስ ኃላፊዎች በሸዋ ሮቢት ፌዴራል ማረሚያ ቤት ከሴፕቴምበር (መስከረም) እስከ ኖቬምበር 2016 (ህዳር 2009) ባለው ጊዜ ውስጥ ስቃይ ማድረስን ጨምሮ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ፈጽመዋል። ታሳሪዎች ለኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እንደገለጹት በሸዋ ሮቢት እስር ቤት ያሉ ባለሥልጣናት የኤሌክትሪክ ንዝረትን፣ ከፍተኛ ድብደባ/ግርፊያን፣ በብልት ላይ ከባድ የውሃ ላስቲክ ማንጠልጠልን፣ በካቴና እና እስረኞችን ከአልጋ ጋር ማሰር እና በውሃ ውስጥ መዝፈቅን ይፈጽሙ እንደነበር ገልጸዋል። የእስልምና ዕምነት ተከታይ የሆኑ ታሳሪዎች እንዳሉት ሹሞቹ ጸረ-ሙስሊም ቃላትን ከፍ ባለ ድምጽ ይናገሩ እና ይበልጥ ይተነኩሷቸው፣ ያስፈራሯቸው እንዲሁም እምነት ላይ ያነጣጠሩ ማስፈራሪያዎችን ያደርጉባቸው እንደነበር ተናግረዋል። አስራ ሁለት ታሳሪዎች እንደተናገሩት ደግሞ ፖሊሶች እነርሱን ነጥለው አውጥተው ከሴፕቴምበር 22 (መስከረም 12) እስከ ኖቬምበር 19 (ህዳር 10) ቀን 2016 (2009) በካቴና ጠፍረው ከአልጋቸው ጋር አስረዋቸው ነበር። ኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ባካሄደው ምርመራ በ16 ታሳሪዎች ላይ በርካታ የአካል ጉዳቶች መድረሱን በማስረጃ አረጋግጧል። ከእነዚህ ጉዳቶች መካከል በእጆች እና እግሮች ላይ ጥልቅ ጠባሳዎች መኖራቸው፣ የተሰበሩ ጣቶች፣ ለረጅም ጊዜ በካቴና መታሰር የፈጠረው ምልክት፣ በጀርባ ላይ የግርፋት ምልክቶች፣ የተነቀሉ ጥፍሮች፣ የተሰበሩ ክንዶች እና በጭንቅላት ላይ የደረሱ ጉዳቶች ይገኙባቸዋል። መርማሪ ቡድኑ እነዚህን ምልክቶች እያንዳንዱ ታሳሪ ወደ እስር ቤት በገባበት ጊዜ ከተመዘገቡ መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ሲመለከት ጉዳቶቹ የደረሱት በእስር ቤት ውስጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ችሏል።

በዲሴምበር 2017 (ታህሳስ 2010) በዋለ የፍርድ ቤት ችሎት ታሳሪዎች ለፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በሸዋ ሮቢት 176 ታሳሪዎች ስቃይ እና ሰቆቃ የተፈጸምባቸው ሲሆን ሪፖርቱ የቀረበው ስለ 16 ታሳሪዎች ብቻ በመሆኑ ቅር መሰኘታቸውን ገልጸዋል። ከዚህም ሌላ ሪፖርቱ የእስር ቤቱን አስተዳዳሪዎች እና የፖሊስ አባላት ለተፈጸመው የመብት ጥሰት ተጠያቂ አለማድረጉ ትክክል አይደለም በሚል ተቃውሞ አቅርበዋል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሪፖርቱ ኃላፊነቱን የሚወስደውን አካል ሳይገልጽ መቅረቱ የማረሚያ ቤት ሪፎርም አክቲቪስቶች (የለውጥ አቀንቃኞች) በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ተዓማኒነት ላይ ጥያቄ እንዲያነሱ አድርጓቸዋል።

በጁላይ (ሐምሌ) ወር ሂውማን ራይትስ ዎች (HRW) በ2011 (2004/2005) እና በዚህ ዓመት መጀመሪያ መካከል በጅግጅጋ ማዕከላዊ እስር ቤት የተፈጸሙ የማሰቃየት ተግባራት፣ የመድፈር፣ ለረጅም ጊዜ በዘፈቀደ የማሰር እና ኢ-ሰብዓዊ የእስር ቤቱን ሁኔታዎች በማስመልከት ሪፖርት አቅርቧል። ብዙዎቹ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የቀድሞ የእስር ቤቱ ታቃቢዎች ታሳሪዎች በፖሊሶች ስቃይ ከደረሰባቸው በኋላ በእስር ቤት ውስጥ ሕይወታቸው ሲያልፍ ተመልክተናል ብለዋል። የቀድሞ እንስት ታሳሪዎች ደግሞ በርካታ ሴቶች መደፈራቸውን ሪፖርት አድርገዋል። የእስር ቤት የጥበቃ አባላት እና የክልሉ ልዩ ኃይል በክልሉ ሹሞች አግባቢነት እስረኞችን ያሰቃዩ ነበር ተብሏል። በሂውማን ራይትስ ዎች ሪፖርት መሠረት እስር ቤቱን የሚቆጣጠረው አልነበረም ለማለት ይቻላል። በጅግጅጋ እስር ቤት (በሌላ መጠሪያ ስሙ ጄል ኦጋዴን ተብሎ የሚታወቅ) ይፈጸም የነበረው የመብት ጥሰት ዑደት፣ ሰብዓዊ ክብርን የሚነካ አያያዝ፣ እስር ቤቱ ለመያዝ ከሚችለው በላይ በእስረኞች መጨናነቁ፣ በቂ ምግብ አለመገኘቱ፣ እስረኞች እንቅልፍ እንዳያገኙ መደረጉ እና የጤና እንክብካቤ አለመኖሩ መንግሥት ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት የነበረው የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ONLF/ኦብነግ) ደጋፊዎችን በጋራ የመቅጣት አቅጣጫ አካል ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም በመንግሥት አሸባሪ ድርጅት ተብሎ ነበር። ይህ ፍረጃ ከጁን ወር ጀምሮ ቀርቷል።

ከበርካታ ምንጮች በተገኙ መረጃዎች መሰረት በይፋ በሚታወቁ እስር ቤቶች፣ ይፋዊ ባልሆኑ ማቆያዎች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በቂሊንጦ የፌደራል መንግሥት እስር ቤት በጠቅላላ የታሳሪዎቸች አያያዝ አግባብነት የሌለው እንደሆነ ተዘግቧል። የፖሊስ መርማሪዎች ከታሳሪዎች ቃል ለማወጣጣት በአካላዊ እና በሥነ ልቦናዊ ስቃይ ተጠቅመዋል።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ከሥልጣን ከመልቀቃቸው በፊት ኢሕአዴግ በጃንዋሪ 3 ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት መንግሥት በአዲስ አበባ የሚገኘውና ባለፉት ዓመታት በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞበታል የሚባለው የፌደራል መንግሥት የምርመራ እና

የእስር ተቋም ኤፕሪል 6 (መጋቢት 28) መዘጋቱን አሳውቋል። ባለሥልጣናትም በማዕከሉ የሚገኙ ታሳሪዎችን ወደ ሌላ እስር ቤት አስተላልፈዋቸዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው ሪፖርት፣ በላይቤሪያ በሰላም አስከባሪነት ለተባበሩበት መንግሥታት ተልዕኮ ከተሰማሩ ኢትዮጵያዊያን መካከል ከአንዷ የወሲብ ጥቃት እና መጠቀሚያ የመድረግ ሪፖርት ደርሶታል። በተባበሩበት መንግሥታትም ሆነ በኢትዮጵያ የወሲብ መጠቀሚያውን ጉዳይ (የወሲብ መጠቀሚያ ግንኙነት) በተመለከተ የሚካሄደው ምርመራ በእንጥልጥል ላይ ነው።

## እስር ቤት እና የማቆያ ማዕከል ሁኔታዎች

የእስር ቤት እና የማቆያ ቦታዎች ሁኔታዎች እጅግ አስቸጋሪ እና አንዳንዶቹ እንዲያውም ለሕይወት አስጊ ሆነው ታይተዋል። የጸጥታ ኃይሎች በማቆያዎች፣ በወታደራዊ ተቋማት እና በፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ በእስረኞች ላይ አካላዊ ጥቃት ማድረሳቸው ሪፖርት ተደርጓል። ካጋጠሙ ችግሮች መካከል እስር ቤቶቹ ካላቸው የመያዝ አቅም በላይ በእስረኞች መጨናነቃቸው፣ በቂ ምግብ እንዲሁም ውሃ፣ ንጽሕናና የሕክምና እንክብካቤ አለመኖር ይጠቀሳሉ። ፍርድ ቤት ከመቅረብ በፊት እስረኞች በፖሊስ ጣቢያ ይቆያሉ፤ የፖሊስ ጣቢያዎች ሁኔታ አንዱ ከሌላው እጅግ የተለየ ሲሆን፣ የንጽሕና ሁኔታ ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር ፖሊሶች እስረኞችን የሚይዙበት ሁኔታ የሙብት ጥሰት የሞባለት ነው።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ጊዜ፣ መንግሥት በአዲስ አበባ፣ ሐዋሳ፣ ድሬዳዋ፣ ነቀምቴ፣ ባሕር ዳር እና ሰመራ የእስረኞችን ማቆያዎች ይከታተል ነበር። በማርች (መጋቢት) ወር፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አጣሪ ቦርድ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ኮማንድ ፖስት ከስድስቱ ዞኖች 1,107 ግለሰቦችን ማሰሩን አሳወቀ። እነዚህ ሰዎች የታሰሩባቸው መንስኤዎች ተብለው በመንግሥት የተገለጹት ምክንያቶች፡- ግድያ፣ የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ማውደም፣ መንገድ መዘጋት፣ የመንግሥት ሰነዶችን ማጥፋት፣ ሕገወጥ የሙሣሪያ ዝውውር እንዲሁም የብሔር ግጭትን ማነሳሳት የሚሉ ናቸው። ሁኔታዎች ከቦታ ቦታ የሚለያዩ ቢሆኑም ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ታሳሪዎች የታሰሩባቸው ቦታዎች የምግብ፣ የውሃ፣ የንጽሕናና የጤና እንክብካቤ እጥረት የጋራ ጉድለቶቻቸው ነበሩ።

<u>አካላዊ ሁኔታዎች</u>፡- ከፍተኛ መጨናነቅ የተለመደ ነው፤ በተለይ በእስር ቤት መኝታ ክፍሎች ችግሩ በሰፊው ተስተውሏል። ለምሳሌ በ2016 (2008/2009) የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በሸዋ ሮቢት የሚገኘውን የፌደራል መንግሥት እስር ቤት ክፍሎች ጎብኝቶ፣ የክፍሉ

ሁለት ትንንሽ መስኮቶች በግምት 40 ካሬ ሜትር (430 ካሬ ጫማ) ስፋት ላለው ክፍል አየር ለማስገባት በቂ አለመሆኑን ታዝበዋል፤ በመሆኑም በዚህ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ 38 ታሳሪዎች እጅግ አነስተኛ ነበር። የእስር ቤቱ ኃላፊዎች አንዳንድ ጊዜ ወጣት ጥፋተኞችን ከአዋቂዎች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ያስራሉ። የእስር ቤቱ አስተዳዳሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ወንዶችን እና ሴቶችን ለይተው የሚያስሩ ቢሆንም አንዳንድ ማዕከሎች ውስጥ መደባለቅ ተከስቷል።

መንግሥት ለምግብ፣ ውሃ እና የጤና እንክብካቤ በቀን በግምት ዘጠኝ ብር ($0.32) የመደበ ሲሆን፣ ይህ የገንዘብ መጠን በአገሪቱ ዙሪያ ይለያያል። ከዓለም ባንክ በተገኘ መረጃ መሰረት የአገሪቱ አጠቃላይ የነፍስ ወከፍ ምርት በቀን $1.50 ነው። በርካታ እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው በየዕለቱ ምግብ ስለሚቀርብላቸው ወይም በአካባቢው ካሉ የምግብ አገልግሎት ሰጪዎች በመግዛት የመንግስትን አቅርቦት ይደግፋሉ። ሪፖርቶች እንደገለጹት የእስር ቤት ኃላፊዎች አንዳንድ እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው ምግብ እዳያገኙ ክልከላ በማድረጋቸው ጠያቂዎቹ ዘመዶቻቸው የት እንደታሰሩ አያውቁም። ሕክምና በፌደራል እስር ቤቶች አስማማኝ አይደለም፤ በክልል እስር ቤቶች ደግሞ ከሞላ ጎደል የማይታሰብ ነው። ለእስረኞች የሚቀርብ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ከፍተኛ እጥረት አለ። የውሃ እጥረት የንጽህና ጉድለት እንዲንሰራፋ አድርጓል፤ አብዛኞቹ እስር ቤቶች ተገቢ የንጽሕና መስጫ ተቋማት የሏቸውም። ብዙዎቹ ታሳሪዎች ከፍተኛ የጤና ችግር እያለባቸው ያገኙት ሕክምና አነስተኛ ነው አሊያም ምንም ዓይነት ሕክምና አልተደረገላቸውም። የእስር ቤቱ ኃላፊዎች አንዳንድ እስረተኞች ሕክምና እንዳያገኙ ከልክለዋል የሚልም ሪፖርት አለ።

የፖለቲካ እስረኞች ጠያቂዎች እና ሌሎች ምንጮች እንደገለጹት የፖለቲካ እስረኞች ከሌሎች እስረኞች የተለየ አያያዝ ያጋጥማቸዋል። በዚህ ረገድ ከቀረቡት አቤቱታዎች መካከል ተገቢ ሕክምና እና መድኃኒት የማይገኝ መሆኑ፣ መጽሐፍት ወይም ቴሌቪዥን አለመኖሩ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዳይደረግ የሚጣል ክልከላ ይገኙባቸዋል።

<u>አስተዳደር</u>፡- በጁላይ (ሐምሌ) ወር የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በፌዴራል እስር ቤቶች የመብት ጥሰቶች ይፈጸማሉ ብሎ ባሰራጨው ዘገባዎች መነሻ መንግሥት አምስት የፌደራል ማረሚያ ቤቶችን ባለሥልጣናት አባሯል። በእስር ቤቶች የጥበቃ አባላት እንግልት የደረሰባቸው እስረኞች ያጋጠማቸውን እንግልት ለእስር ቤቱ አስተዳዳሪዎችም ሆነ ለእምባ ጠባቂ አካላት ለማሳወቅ እንዳይችሉ ተደርገዋል። በአንዳንድ እስር ቤቶች የሕግ እገዛ መስጫ ተቋማት አሉ። በክልል ደረጃ እነዚህ ተቋማት ከፍርድ ቤቶች፣ ከእስር ቤት እና ከሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣናት ወይም መሥሪያ ቤቶች ጋር ጥሩ የሥራ ግንኙነት አሏቸው። የእስር ቤት ኃላፊዎች ለአንዳንድ ታቃቢዎች ያለሳንሱር አቤቱታዎቻቸውን ለፍርድ ቤት

እንዲያቀርቡ ቢፈቅዱላቸውም፣ አንዳንድ ጊዜ ፍርድ ቤቶች እንዲህ ያሉትን አቤቱታዎች ለመስማት ፈቃደኞች አይደሉም።

ሕጉ እስረኞች እንዲጠየቁ ይፈቅዳል። ነገር ግን ባለሥልጣናት አንዳንድ ክስ የቀረበባቸው ተከሳሾች ከጠበቆቻቸው እና አባል ከሆኑባቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ጋር እንዳይገናኙ ክልከላ አድርገውባቸዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ፖሊሶች በምርመራ ላይ ያሉ እስረኞች ከቤተሰብ አባላት እና ከጠበቆቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ክልከላ አድርገዋል። የእስር ቤት ደንቦች እንደሚሉት በሽብር ወንጀል የተከሰሱ ታሳሪዎች ጠበቆች በቀን መጠየቅ ወይም ማነጋገር የሚችሉት አንድ እስረኛ ብቻ ነው፤ ያውም በረቡዕ እና በዓርብ ቀናት ብቻ። የእስር ቤቱኃላፊዎች በሽብር ድርጊት የተከሰሱ ሰዎች ከቤተሰብ አባላት ጋር እንዳይገናኙ እገዳ ጥለዋል።

የእስር ቤት ኃላፊዎች እስረኞች የኃይማኖት ሥርዓት እንዲፈጽሙ ቢፈቅዱም፣ ይህ ፈቃድ ግን ከአንድ እስር ቤት ወደ ሌላ እስር ቤት እንዲሁም በአንድ እስር ቤት ውስጥ እንኳን የአንዱ እስር ክፍል ከሌላው የተለየ ነው። የእስር ቤት ኃላፊዎች ታሳሪዎች የሚጸልዩበት በቂ ቦታ ከልክለዋል የሚል አቤቱታ ቀርቧል።

<u>ገለልተኛ ቁጥጥር</u>፡- ዓለም ዓቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (ICRC) የዓመታዊ መደበኛው ሥራው አካል በሆነ መልኩ በመላው አገሪቱ የሚገኙ ታሳሪዎችን ጎብኝቷል። አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በነበረበት ወቅት ኮሚቴው እስር ቤቶቹን ለመጎብኘት የነበረው ፈቃድ የተገደበ ነበር። ነገር ግን በጁን ወር አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሲነሳ፣ ዓለም ዓቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ ጉብኝቱን በብዛት ለማድረግ ችሏል። መንግሥት ሌሎች የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እስር ቤቶቹን እንዲጎበኙ አልፈቀደም።

የክልል ባለሥልጣናት ሦስተኛ ወገኖች በሌሉበት የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ከእስረኞች ጋር እንዲገናኙ ፈቅደዋል። የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የፌዴራል እና የክልል እስር ቤቶችን ጎብኝተዋል፤ ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አለ በሚል ይቀርብ ስለነበረውም ክስ ከእስር ቤት አስተዳዳሪዎች እና ከእስረኞች ጋር ቃለ ምልልስ አድርገዋል። ጀስቲስ ፎር ኦል - ኢትዮጵያ ፕሪዘንስ ፌሎሺፕ (JPA-PFE) በአገሪቱ ዙሪያ የተለያዩ ማረሚያ ቤቶችን እና ማቆያ ተቋማትን ለመጎብኘት ችለዋል።

## መ. በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል ወይም ማሰር

ሕገ መንግሥቱ እና ሌሎች ሕጎች ሰዎች በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር እንዳይውሉ እና እንዳይታሰሩ ክልከላ ያደርጋሉ፤ ሆኖም ግን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሕግ አስከባሪ አካላት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማግኘት ሳያስፈልግ ሰዎችን በቁጥጥር ስር እንዲያውሉ እና በመደበኛ አሰራሮች ከሚፈቀደው በላይ አስረው እንዲያቆዩ ፈቅዷል። ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር በተያያዘ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዘፈቀደ ታስረዋል የሚሉ ሪፖርቶች ቀርበዋል፤ በተለይ ደግሞ የተቃውሞ ሰልፈኞች፣ መምህራን፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ ሙዚቀኞች፣ ነጋዴዎች፣ የጤና ባለሙያዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ልጆች እና ሌሎች ታስረዋል።

## የፖሊስ እና የጸጥታ ተቋማት ሚና

የፌዴራል ፖሊስ ከኦክቶበር (ጥቅምት) ወር ጀምሮ ተጠሪነቱ ለሰላም ሚኒስቴር ሲሆን፣ በፓርላማ ቁጥጥር ስር ሥራዎቹን ያከናውናል። የዚህ ቁጥጥር አድማስ የተወሰነ ነበር። ዘጠኙም ክልሎች ክልላዊ ወይም ልዩ የፖሊስ ኃይል ያላቸው ሲሆን፣ የፖሊስ ኃይሉ ተጠሪነቱ ለሲቪል ባለሥልጣናት ነው። በአገሪቱ በአጠቃላይ የሚንቀሳቀሱ የአካባቢ ሚሊሺያ አባላት ከክልል ፖሊስ፣ ከፌዴራል ፖሊስ እና ከመከላከያ ሰራዊት ጋር ያላቸው የሥራ ግንኙነት የላላ እና ግንኙነታቸውም የተለያየ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሚሊሺያዎች የገዢው ፓርቲ ተቀጽላዎች ሆነው ያገለግላሉ። የአካባቢ ሚሊሻዎች ባሉባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ በተለይ ደግሞ በገጠራማ አካባቢዎች፣ መደበኛ የጸጥታ ጉዳዮችን ይከታተላሉ። የአካባቢ የመንግሥት ባለሥልጣናት ለተመረጡ የሚሊሺያ አባላት መሠረታዊ ሥልጠናዎችን ይሰጣሉ። የሚሊሺያ አባላት ደግሞ በማኅበረሰቡ እና በአካባቢው ፖሊስ መካከል እንደ ድልድይ ያገለግላሉ፤ መረጃ ይሰጣሉ፣ ደንቦችን ያስፈጽማሉ። በአስቸኳይ አዋጅ ጊዜ ወታደሩ ውስጣዊ ደህንነትን በተመለከተ ሰፊ ሚና ተጫውቷል።

በሕግ ሳይጠየቁ መቅረት፣ በተቃውሞ ሰልፈኞች ላይ ግድያ እና ሌሎች ጥቃቶች መፈጸምን ጨምሮ ከሕግ ተጠያቂነት ውጪ መሆናቸው ችግር ሆኖ ቀጥሏል። በፖሊስ ኃይሎች ዘንድ የውስጥ ምርመራ ሂደት ተካሂዷል፤ ነገር ግን ባለሥልጣናት እንዳሉት ይህ በቂ አይደለም። ውስጣዊ አሰራሮች የሚሻሻሉባቸው እና ዘመናዊ የሚደረጉባቸው ቀጣይ ጥረቶች አሉ። በአስቸኳይ አዋጅ ጊዜ ፌዴራል ፖሊስ የፈጸማቸው ጥፋቶች ካሉ እነርሱን ለማጣራት ውስጣዊ ምርመራ እየተካሄደ ስለመሆኑ ለሕዝብ ይፋ የተደረጉ ማስረጃዎች ወይም ሰነዶች የሉም። መንግሥት በአካባቢ የጸጥታ ኃይሎች ስለተፈጸሙ ጥፋቶች ለምሳሌ በዘፈቀደ ስለ ማሰር እና ሲቪሎች ላይ ስለተፈጸሙ ድብደባዎች ወይም ግርፋቶች የተካሄዱ ምርመራዎችን ውጤቶች  መረጃ መስጠቱ እምብዛም ነው።

መንግሥት ለፖሊስ እና ለመከላከያ ሰራዊት አባላት በሰብዓዊ መብቶች ላይ ለሚሰጥ ስልጠና የሚያደርገው ድጋፍ የተወሰነ ነው። ከሕገ መንግሥቱ እና ከዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች የተወሰዱ ይዘቶችን በማከል በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ለመሻሻል እና ይበልጥ ሙያዊ ለማድረግ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እገዛ አግኝቷል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል በአዲስ አበባ በሚገኘው የሰላም ድጋፍ ስልጠና ማዕከል በተደጋጋሚ በሰብዓዊ መብቶች፣ በሲቪሎች ጥበቃ፣ በጾታ ላይ ስለተመሰረተ ጥቃት እና በሌሌሎች ጉዳዮች ላይ ስልጠና ወስዷል።

## በቁጥጥር ስር የማዋል ሥርአቶች እና የታሳሪዎች አያያዝ

ሕገ መንግሥቱ እና ሌሎች ሕጎች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ ወይም እንደ አካባቢው ሁኔታ እና የመገናኛ ዘዴዎች በሚፈቅዱት መጠን ከተገለጸው ጊዜ ብዙም ሳይዘገይ ፍርድ ቤት ቀርበው ክስ እንደሚመሰረትባቸው ይደነግጋል። ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድ የሚወስደው ጊዜ በ48 ሰዓቱ ውስጥ አይካተትም። ከፍ ባለ የወንጀል ድርጊት ለተጠረጠሩ ሰዎች ምርመራ በመካሄድ ላይ ሳለ ክስ ሳይመሰረት ለ14 ቀናት በእስር እንዲቆዩ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን፣ ይህ የ14 ቀናት ጊዜ በየወቅቱ ሊታደስ ይችላል። ፍርድ ቤቶችም ክስ ሳይመሰረት ምርመራዎች ከ14 ቀናት በላይ እንዲቀጥሉ ለደህንነት ኃላፊዎች ሲፈቅዱ ቆይተዋል።

በጸረ-ሽበር አዋጅ ስር ፖሊስ ምርመራ እያካሄደ ሳለ ተጠርጣሪዎችን በ28 ቀናት ለተከፋፈሉ ጊዜያት ቢበዛ እስከ አራት ወራት ጊዜ ክስ ሳይመሰርት በእስር ሊያቆይ ይችላል። ሕጉ "ከፍተኛ ወንጀሎች" በሚፈጸሙ ጊዜ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማሰርን ይፈቅዳል። እነዚህም ወንጀሎችን ሲፈጽሙ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ወይም ወንጀል ለመፈጸም በመሞከር ላይ ያሉ ወይም ወንጀሉን እንደፈጸሙ ወዲያውኑ የተደረሰባቸው ተጠርጣሪዎችን ያካትታል።

በይፋ በሚታወቁ ተቋማት ካልሆነ በቀር እስረኞችን ማሰር የተከለከለ መሆኑ በሕጉ ተደንግጓል፤ ሆኖም ግን የአካባቢ ታጣቂዎች እና ሌሎች መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ ሕግ አስከባሪ አካላት ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ይፋዊ ያልሆኑ የእስር ማዕከላት ነበሯቸው።

ውጤታማ የዋስትና ሥርዓት ተግባራዊ ተደርጎ ነበር። ሆኖም ግን በሽበር ወንጀል፣ በግድያ፣ በአገር ክህደት እና ሙስና ወንጀሎች ክስ ለተመሰረተባቸው ሰዎች ዋስትና የለም። በሌሎች ጉዳዮች ደግሞ ፍርድ ቤቶች ከብር 500 እስከ ብር 10,000 ($18 and $357) የዋስትና ገንዘብ የሚወስኑ ቢሆንም፣ አብዛኛዎቹ የአገሪቱ ዜጎች ይህንን ያህሉን የዋስትና ገንዘብ መክፍል

የሚችሉ አይደሉም። በግል ጠበቃ ማቆም ለማይችሉ ተከሳሾች መንግሥት ጠበቃ ያቆምላቸዋል፤ ሆኖም ግን ተከሳሾች እንዲህ ያለውን አገልግሎት የሚያገኙት ጉዳዮቻቸው ወደ ፍርድ ቤት ሲሄዱ እንጂ ወሳኝ በሆነው ቅድመ የፍርድ ሂደት ወቅት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በአንድ ጉዳይ ለበርካታ ተከሳሾች አንድ ጠበቃ ሲቆም ታይቷል። አንዳንድ ታሳሪዎች በምርመራ ላይ እያሉ በእስር ላይ ቢሆኑም፣ ከሕግ አማካሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት የተገደበ እንዲሆን ወይም ጭራሹንም እንዳይገናኙ ተደርጓል፤ ስለጤናቸው ሁኔታ ሙሉ መረጃ አልሰጡም፣ በቤተሰቦቻቸው እንዲገበኙም አልፈቀዱም። አንዳንድ ጊዜ የእስር ቤት ኃላፊዎች እስረኞችን ከሌሎች ለይተው ብቻቸውን ለሣምንታት አስረው ያቆያሉ፤ እንዲሁም ሲቪል ሰዎችን ይፋ ላልተደረገ ጊዜ በቁም ያስራሉ።

ሕገ መንግሥቱ እንደሚያዘው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎችን የስም ዝርዝር በተያዙ አንድ ወር ውስጥ ኃላፊዎች ማሳወቅ አለባቸው። በእርግጥ በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች ስም ዝርዝር የተገለጸ ቢሆንም፣ የአንድ ወሩ የጊዜ ገደብ ያልተከበረባቸው ወቅቶች ነበሩ። ሲቪሎች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎችን ዝርዝር በቀላሉ ማግኘት የማይችሉባቸው ጊዜያትም ነበሩ።

<u>በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል</u>፡- ባለሥልጣናት አዘውትረው የተቃውሞ ሰልፈኞችን፣ ጋዜጠኞችን እና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ሲያስሩ ቆይተዋል። የጸጥታ ኃይሎች ሰዎችን በዘፈቀደ ስለማሰራቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ሪፖርቶች አሉ።

ማርች 25 (መጋቢት 16) የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች እስክንድር ነጋን እና ተመስገን ደሳለኝን በቁጥጥር ስር አዋሉ፤ ማህሌት ፋንታሁን፣ በፈቃዱ ኃይሉ፣ ዘላለም ወርቃገኘሁ እና ፈቃዱ ማህሌተወርቅ የተባሉ ጦማርያን እንዲሁም አንዷለም አራጌ፣ አዲሱ ጌታነህ፣ ይድነቃቸው አዲስ፣ ተፈራ ተስፋዬ እና ወይንሸት ሞላ የተባሉ አክቲቪስቶችም አዲስ አበባ ውስጥ ባለው በጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ መኖሪያ ቤት በተገኛችሁበት ጊዜ ተገቢ ያልሆነ ብሔራዊ ባንዲራ ይዛችኋል በሚል ታሰሩ። ፖሊስ በመጀመሪያ እነዚህን 11 ታሳሪዎች በአዲስ አበባ ጀሞ አካባቢ ወደሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ወሰዳቸው። በምሽትም ጎተራ ፔፕሲ አካባቢ ወደሚገኝ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ አዘዋወራቸው። በኤፕሪል 5 (መጋቢት 27) ደግሞ፣ ባለሥልጣናቱ በአዲስ አበባ ይገኙ የነበሩትን እነዚህን ታሳሪዎች ክስ ሳይመሰርት ለቋቸዋል።

በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አጣሪ ቦርድ ማርች 31 (መጋቢት 22) በወጣ ሪፖርት መሠረት፣ የጸጥታ ኃይሎች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተላልፈዋል በሚል የተጠረጠሩ 1,107 ግለሰቦችን አስሯል።

<u>የቅድመ ፍርድ ቤት ሂደት/የምርመራ ጊዜ እስር</u>፡- አንዳንድ ታሳሪዎች ክስ ሳይመሰረትባቸው ወይም ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለዓመታት በእስር ላይ መቆየታቸውን ይገልጻሉ። ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በእስር ላይ የቆዩ ታሳሪዎች ብዛት በመቶኛ እና አማካይ የእስር ጊዜያቸውን የሚያሳይ መረጃ የለም። ረጅም ጊዜ የፈጀ የክስ ሂደት፣ ከፍተኛ የታሳሪዎች ቁጥር፣ የፍርድ አካላት አቅም አናሳ መሆን እና የባለሙያዎች እጥረት የፍርድ ቤት ጉዳዮች እንዲጓተቱ፣ አንዳንድ ጊዜ ለዓመታት እልባት ሳያገኙ እንዲቆዩ ምክንያት ይሆናሉ። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ደንቦች የአስቸኳይ አዋጁ ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ ታሳሪዎችን ካለፍርድ ቤት ተዕዛዝ በእስር እንዲቆዩ ይፈቅዳሉ። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሲጠናቀቅ፣ በበርካታ መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በቀጠሮ እና የክስ መመስረትን በመጠባበቅ በእስር ላይ ቆይተዋል።

<u>ታሳሪዎች በፍርድ ቤት እስርን በመቃወም መገዳደር ስለመቻላቸው፡-</u> በሕጉ መሠረት ሹሞች በቁጥጥር ስር ያዋሏቸውን ሰዎች ለምን በቁጥጥር ስር እንዳዋሉ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ ያለባቸው ሲሆን፣ ጊዜውም በክሱ ክብደት ይወሰናል። ሕግ በወንጀል ክስ ለቀረበባቸው ሰዎች ይግባኝ የመጠየቅ መብት ይሰጣል። በዓመቱ ውስጥ ማንም ሰው ከሕግ ውጭ ታስሬያለሁ ብሎ በፍርድ ቤት ክስ የመሰረተ የለም። በሌላ በኩል ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ጋር በተያያዘ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዘፈቀደ መያዛቸው እና መታሰራቸው ሪፖርት ተደርጓል። የወንጀል ሕጉ በሕገ ወጥ መንገድ የታሰሩ ሰዎች ካሣ እንዲከፈላቸው አይደነግግም፡
፡

<u>ይቅርታ</u>፡- የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር እስረኞች እንደሚፈቱ ጃንዋሪ 3 (ታህሳስ 25) ካሳወቁ በኋላ በነበሩት ስድስት ሳምንታት ውስጥ 9,702 ታሳሪዎች በፌደራል እና በክልል መንግሥታት ከእስር ተፈትተዋል። በእነዚህ ሳምንታትም ውስጥ መንግሥት አብዛኛዎቹን ታዋቂ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች እና አክቲቪስቶች (የፖለቲካ አቀንቃኞች) ከእስር እንዲፈቱ አድርጓል።

የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በሽብር እና በሙስና ክስ የቀረበባቸው ወይም ጥፋተኞች የተባሉ 744 ግለሰቦች ክሶች እንዲሰረዙ እና/ወይም ምሕረት እንዲሰጣቸው አድርጓል። ከእነርሱም ውስጥ 576 የሚሆኑት ጥፋተኞች ተብለው በእስር ላይ የነበሩ ናቸው፤ 168 የሚሆኑት ደግሞ በክስ ሂደት ላይ የነበሩ ናቸው። አብዛኞቹ ማለትም ከ500 በላይ የሚሆኑት ሜይ 29 (ግንቦት 21) ቀን ከእስር ቤት ተፈትተው ወጥተዋል። የእስረኞችን መለቀቅ በተመለከተ በመንግሥት የተሰጠው ምክንያት የጥፋተኞቹ መጸጸት፣ ለሕብረተሰቡ ስጋት መሆናቸው መቀነሱ እንዲሁም የፖለቲካው ምኅዳር በቀጣይነት እንዲሰፋ አስተዋጽዖ ማድረግ የሚሉ ናቸው። የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፍተኛ የአመራር አባላት፣ ጋዜጠኞች፣

አክቲቪስቶች እና በሽብርተኝነት እና በሙስና የተከሰሱ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ከእስር ከተለቀቁት መካከል ናቸው።

ሜይ 29 (ግንቦት 21) ፣ ባለሥልጣናት በትውልድ ኢትዮጵያዊ፣ በዜግነት እንግሊዛዊ የሆነውን አንዳርጋቸው ጽጌን ከእስር ፈቱ። አንዳርጋቸው ጽጌ የአርበኞች ግንቦት 7 (PG7) ምክትል ኃላፊ ሲሆን፣ይህ ድርጅት ቀደም ሲል በመንግሥት ሽብርተኛ ተብሎ ተፈርጆ ነበር። በሰኔ ወር "በልዩ ሁኔታ በምሕረት" ከሽብር ድርጅትነት ተሰርዟል። በ2014 በቁጥጥር ሥር የዋሉት አንዳርጋቸው በሁለት ክሶች የዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸው ነበር፤ የሞት ፍርድም ተላልፎባቸው ነበር።

ጁላይ 20 (ሐምሌ 13)፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ በተለያዩ ወንጀሎች በምርመራ፣ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ የነበሩ ወይም ጉዳያቸው አልቆ ጥፋተኛ ለተባሉ ግለሰቦች እና ቡድኖች ምሕረት አደረገ። ሕጉ ከጁን 7 (ግንቦት 30) በፊት በተፈጸሙ ወንጀሎች ጥፋተኛ በተባሉ ሰዎች እና ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚነት አለው። የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ምሕረት እንዲደረግላቸው የሚፈልጉ ሰዎች ከጁላይ 23 (ሐምሌ 16) ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ መመዝገብ አለባቸው ብሏል። ኦገስት 23 (ነሐሴ 17) ቀን ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በአራት ፌዴራል እስር ቤቶች የሚገኙ 650 ታሳሪዎችን የይቅርታ ወይም የምሕረት ተጠቃሚ አድርጓል። በምሕረት አዋጁም መሠረት መንግሥት ከእነዚህ እስረኞች መካከል ከ200 በላይ ለሚሆኑት ምህረት ሰጥቷል።

በሴፕቴምበር ወር ለረጅም ጊዜ በቆየው በኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ይቅርታ የማድረግ ልማድ መሠረት አራት የክልል መንግሥታት 8,875 እስረኞችን ለቅቀዋል። አንድ ሦስተኛ ያህል የእስር ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ታሳሪዎች፣ ልጆች ያሏቸው የሴት እስረኞች፣ አዛውንቶች፣ እንዲሁም ከፍተኛ የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች በይቅርታው ተጠቃሚ ሆነዋል። የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው እና በሙስና፣ በጠለፋ ወይም በመድፈር ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉ ፍርደኞች በኢትዮጵያ አዲስ ዓመት የሚሰጠው ይቅርታ ተጠቃሚ አይሆኑም።

## ሠ. በፍትሐዊ ክፍት ችሎት የመዳኘት መብትን መከልከል

ሕጉ ፍርድ ቤቶች ገለልተኛ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል። የፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው በገለልተኝነት የሚሰሩ ቢሆኑም፣ የወንጀል ፍርድ ቤቶች ግን ደካማ፣ በሥራ ጫና የተጨናነቁ እና የፖለቲካ ጫና የሚደርስባቸው ናቸው።

## የፍርድ ስራዓቶች

በሕገ መንግሥቱ መሠረት ክስ የቀረበባቸው ሰዎች በክፍት ችሎት በፍትሐዊ የፍርድ ሂደት ውሳኔ የማግኘት መብት ስላላቸው፣ የፍርድ ሂደቱም ተገቢ ካልሆነ መዘግየት ነጻ የመሆን፣ ተከሳሾች ነጻ ተደርገው የመቆጠር መብት፣ በራሳቸው ምርጫ ጠበቃ የማቆም፣ ይግባኝ የመጠየቅ፣ በራሳቸው ላይ ያለመመስከር መብት፣ ምሥክሮች እና የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ እንዲሁም ለዓቃቤ ሕግ ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው። በሕጉ እንደተቀመጠው ተከሳሾች በሚረዱት ቋንቋ የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተሉ አስተርጓሚ መመደብ እንዳለበት ይደነግጋል። የፌደራል ፍርድ ቤቶች ለዋና ዋና ቋንቋዎች አስተርጓሚዎች አሏቸው፤ ሌሎች ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ተከሳሾች ደግሞ አስተርጓሚዎች እንዲቀጥሩ ሕጉ ያዛል።

ነገር ግን ታሳሪዎች እነዚህ መብቶች ሁሉ ተከብረውላቸዋል ማለት አይደለም። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ጊዜ መከላከያ ጠበቆች በቂ ክርክር ለማቅረብ ሳይዘጋጁ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ። ፍርድ ቤቶች ሁል ጊዜ ተከሳሾችን ነጻ አድርገው አያዩም፤ ተከሳሾች የራሳቸውን ጠበቃ እንዲቀጥሩ አይፈቅዱም፤ ጊዜውን የጠበቀ መከላከያ አያቀርቡም ወይም በመንግሥት ዘንድ የሚገኙ ማስረጃዎች እንዳይቀርቡ ክልከላ ያደርጋሉ። ተሰካሾች ብዙ ጊዜ የፍርድ ሂደት እስኪጀመር ድረስ በተለይ የተከሰሱበትን ጉዳይ አያውቁም። ኃላፊዎች ከታሳሪዎች መረጃ ለማግኘት ወይም የተከሳሽነት ቃል ለመቀበል ሲሉ የኃይል ድርጊት ስለመፈጸማቸው ዘገባዎች ቀርበዋል።

የፌደራል የመንግሥት ጠበቆች መሥሪያ ቤት ለችግረኛ ተከሳሾች የሕግ ምክር አገልግሎት የሰጠ ሲሆን፣ በጠበቆች እጥረት ምክንያት የአገልግሎቱ ስፋት እና ጥራት ግን በቂ አይደለም፡ ፡ አንድ በመንግሥት ተቀጥሮ ለተከሳሾች አገልግሎት የሚሰጥ ጠበቃ ከ100 በላይ ጉዳዮችን የሚይዝ በመሆኑ፣ ለአንድ ጉዳይ በርካታ ተከሳሾችን ሊወክል ይችላል። በርካታ የነጻ ሕግ አገልግሎት መስጫዎች በተለይ ደግሞ በዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ሆነው የሕግ አገልግሎት ሰጥተዋል። በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ ለምሳሌ የሕግ ተማሪዎች እና የሕግ መምህራን ያለክፍያ የሕግ አገልግሎት እንዲሰጡ ሕጉ ይፈቅድላቸዋል። የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ወይም ሌላ ደረጃ የወጣለት የወንጀል ጥብቅና ደንብ ግን የለም።

በሕገ መንግሥቱ ኃይማኖታዊ እና ባሕላዊ የፍርድ ሥርዓቶች ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል። በገጠር አካባቢ የሚኖሩ በርካታ ዜጎች ለመደኛ የፍርድ ሥርዓቶች ያላቸው ተደራሽነት የተገደበ ሲሆን፣ አለመግባባቶችን ለመፍታት በአብዛኛው የሚተማመኑት በባሕላዊ የፍርድ አካሄዶች ነው።በሕጉ እንደተቀመጠው በአለመግባባት ላይ ያሉት ወገኖች ጉዳያቸው በባሕላዊ ወይም

በኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት እንዲታይላቸው መጀመሪያ መስማማት አለባቸው፤ አንዱ ተከራካሪ ወገን ግን በማንኛውም ጊዜ በመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል። የሸሪዓ (እስላማዊ) ፍርድ ቤቶች ኃይማኖታዊ እና የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ያሉባቸውን የቤተሰብ ጉዳዮች ያያሉ፤ ይህም የሚሆነው ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኞች ከሆኑ ነው። የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከመንግሥት የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ አግኝተዋል። እነዚህ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የእስልምና ተከታይ በሚበዛባቸው በሶማሌ እና አፋር ክልሎች በበርካታ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጥተዋል። ሌሎች ባሕላዊ ሥርዓቶች፣ ለምሳሌ የአገር ሽማግሌዎች በተለይ በተለይ በገጠር አካባቢዎች አገልግሎት ይሰጣሉ። አንዳንድ ሴቶች በባሕላዊ የፍርድ አሰጣጥ ሥርዓቶች ነጻ እና ፍትሐዊ ዕድል እንዳልተሰጣቸው ይናገራሉ። ምክንያቱም  የአካባቢው ባሕል በሽምግልና ጉባዔው እንዳይሳተፉ ስሚከለክላቸው እና አሁንም ድረስ ሊቀረፍ ያልቻለ የጾታ መድልዖ ያለ በመሆኑ ነው።

## የፖለቲካ እስረኞች እና ታቃቢዎች

በዓመቱ መጨረሻ በፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች አልነበሩም፤ ምክንያቱም መንግሥት ክሶቻቸውን ስለሰረዘ እና/ወይም በሽብር እና ሙስና ወንጀል ለተከሰሱ ከአስር ሺህ ለሚልቁ ሰዎች ምሕረት ስላደረገ ነበር።

ባለስልጥጣናት የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) ሊቀመንበር የሆኑትን መረራ ጉዲናን ጃንዋሪ 17 (ጥር 8) ቀን ከእስር ፈተዋል፤ ይህም የሆነው ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ በእርሳቸው ላይ ተመስርቶ የነበረውን በርካታ ክሶች ይዞ የነበረውን የወንጀል ጉዳይ ለመሰረዝ በመወሰኑ ነው፡ ፡ በ2017 (2009/2010) ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በመረራ ጉዲና እና በሌሎች አራት ተከሳሾች ላይ በርካታ ክሶች መስርቶ ነበር፤ በክሱ ከተካተቱት መካከል ብርሃኑ ነጋ እና በውጭ አገር ይንቀሳቀስ የነበረው የኦሮሞ አክቲቪስት ጃዋር መሐመድ ይገኙባቸዋል።

በፌብርዋሪ (በየካቲት) የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በቀሪዎቹ የዞን 9 ጦማርያን ቡድን ናትናኤል ፈለቀ፣ አጥናፍ ብርሃኔ እና በፈቃዱ ኃይሉ ላይ የነበረውን የክስ ሂደት ሰረዘ። በ2017 (2010) ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሦስት ጦማርያን ላይ የተመሰረተውን የሽብር ክስ ሕዝብን ወደ ማነሳሳት ወንጀል ዝቅ አደረገ። ዓቃቤ ሕግ አዲስ አበባን ለማስፋት በወጣው ዕቅድ ላይ ተቃውሞ በማነሳሳት የመሰረተውን ክስ ካነሳ በኋላ ፌብርዋሪ 13 (የካቲት 6) የመንግሥት ባለሥልጣናት የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) ምክትል ሊቀመንበር በቀለ ገርባ እና አብረዋቸው የተከሰሱ ሰዎች ከእስር እንዲለቀቁ አደረጉ።

ሜይ 29 (ግንቦት 21) ቀን፣ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በዳያስፖራው ይንቀሳቀሱ በነበሩት በግንቦት 7 መሪ ብርሃኑ ነጋ እና በኦሮሞው አክቲቪስት ጃዋር መሐመድ እንዲሁም በሚዲያዎቻቸው ማለትም በኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን እና ሬዲዮ እንዲሁም በኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ ላይ የተመሰረተውን ክስ አነሳ።

## የፍትሐ ብሔር ስርዓቶች እና መፍትሔዎች

ዜጎች አቤቱታቸውን ለፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ያላቸው ሲሆን፣ አቤቱታ ሊያቀርቡባቸው የሚችሏቸው ጉዳዮች የሰብዓዊ መብት ጥሰትን እንደሚጨምሩ ይደነግጋል፡ ፡ የሰብዓዊ መብትን ጥሷል የተባለው አካል የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ ተጠቂው ሰው አቤቱታውን መጀመሪያ ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል። ፓርላማው የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንን ያቋቋመው በ2000 (1992) ሲሆን፣ ለኮሚሽኑ ገንዘብ ሲመድብ እና ሥራውንም ሲከታተል ቆይቷል። ኮሚሽኑ ጉዳዮችን ከመረመረ በኋላ ለሚመለከተው የመንግሥት ኤጀንሲ የውሳኔ ሃሳቡን ያቀርባል። ዜጎች አንድም ማስረጃ ማግኘት ባለመቻል፣ አለበለዚያም ይህ ተቋም እንዲህ ባሉት ጉዳዮች ላይ ከመድልዖ ነጻ የሆነ ውሳኔ ሊሰጠን አይችልም በሚል እምነት ማጣት ለተቋሙ አቤቱታ አላቀረቡም።

## ረ. በግል ሕይወት፣ በቤቱሰብ፣ በመኖሪያ ቤት ወይም በደብዳቤ ልውውጥ ላይ በዘፈቀደ ወይም በሕገ ወጥ ሁኔታ ጣልቃ መግባት

በግል ንብረት ላይ ፍተሻ ለማካሔድ አስቀድሞ የፍርድ ቤት ማዘዣ መገኘት እንዳለበት ሕጉ ይደነግጋል። በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት ግን ፍተሻ ለማድረግ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማስፈለጉ ለጊዜው እንዲቀር ተደርጓል። የጸጥታ ኃይሎች ፍተሻ ከማድረጋቸው በፊት ብርበራው ለምን እንደሚደረግ ለግለሰቡ ወይም ለቤተሰቡ ማሳወቅ፣ የሥራ መታወቂያ ማሳየት እና አንድ የማኅበረሰቡ አባል ፍተሻውን እንዲታዘብ ማድረግ አለባቸው። ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁም ውጪ፣ የጸጥታ ኃይል አባላት አንድን ተጠርጣሪ በማሳደድ ላይ ሳሉ ለምሳሌ ወደ አንድ ቤት ቢገባ ወይም በዚያ ቤት ላይ ከተሰራው ወንጀል ጋር በተያያዘ በቤቱ ውስጥ አንድ ነገር ወይም ዕቃ ቢጥል ለዚያ ሲባል ወደ ቤቱ ወይም ቅጥር ግቢው ለመግባት እንደሚችሉ በሕግ ተደንግጓል። ከዚህም ሌላ የፖሊስ አባላት በዚያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሦስት ዓመት በላይ የእስር ቅጣት ሊያስከትል የሚችል ወንጀል ማስረጃ በዚያ ገቢ ውስጥ ተደብቋል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖራቸው ወይም የፍተሻ ትዕዛዝ ከፍርድ ቤት ማግኘት ጊዜ ስለሚፈጅ እና በዚያ ጊዜ ውስጥ ማስረጃው ከዚያ ስፍራ ሊወሰድ ይችላል ብለው ካመኑ ያለፍርድ ቤት

ትዕዛዝ ፍተሻ ማድረግ ይችላሉ። ከዚህ ሌላ የጸረ ሽብር አዋጅ (ATP) የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባይኖር እንኳን የግለሰቦች ቤቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ሊፈተሹ እንደሚችሉ፣ እንዲህ ላለው ብርበራ የፌደራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ወይም በእርሳቸው የተወከለ ሰው ወይም የሽብር ድርጊት ሊጸፈም ስለሚችል ድንገተኛ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነ ፖሊስ መፍቀድ እንዳለበት ሕግ ያዛል።

የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች እና ጋዜጠኞች የስልክ ጠለፋ፣ በሌላ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ በስውር የማዳመጥ፣ ክትትል እንደሚደረግባቸው መጠርጠራቸውን ሪፖርት ሲያደርጉ፣ በመንግሥት የተመደቡ ሰዎች ከዚህ ቀደም በሽብርተኝነት የተፈረጀ ድርጅት አባላት በመምሰል ስልክ ደውለው ሕገ ወጥ ድርጊት እንዲፈጸሙ ሊያግባቧቸው ይሞክሩ እንደነበር ገልጸዋል።

መንግሥት በግለሰቦች እንቅስቃሴ ላይ መረጃ እንዲሰበስቡ በተከፋይ ወሬ አቀባዮች ይጠቀም ነበር። የተቃዋሚ ጎራ አባላት፣ ጋዜጠኞች እና አትሌቶች የገዢው ፓርቲ ሰዎች እና የሚሊሺያ አባላት ወደ ቤቶቻቸው እና መሥሪያ ቤቶቻቸው ሳይጠሩ በመምጣት ማስፈራራት እንደደረሰባቸው ገልጸዋል። እንደዚህ ያሉ የማስፈራራት ድርጊቶች የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይኖር ወደ ቤት ወይም ወደ ሥራ ቦታ መግባት እና ፍተሻ ማካሄድን ያካትታል።

ባለሥልጣናት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ከሥራዎቻው እንዳባረሯቸው እና ከኢሕአዴግ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ነዋሪዎች ሥራ ለማግኘት ከ*ቀበሌዎቻቸው* መሰጠት የሚገባቸውን “የድጋፍ ደብዳቤ” ማግኘት አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው (በክፍል 3፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የፖለቲካ ተሳትፎ የሚለውን ክፍል ተመልከቱ) ዘገባዎች ያመለክታሉ።

## ክፍል 2. የሲቪል መብቶችን ማክበር፣ ከእነርሱም መካከል፡-

### ሀ. ፕሬስን ጨምሮ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣

ሕገ መንግሥቱ እና ሕግ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ እና የፕሬስ መብትን ያከብራሉ፤ ሆኖም ግን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በእነዚህ መብቶች ላይ ገደቦች ተጥለዋል። ስለዚህ ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በፊት የነበረውን ጋዜጠኞችን መተንኮስ እና ማስፈራራት ሕጋዊ ሽፋን አገኘ ማለት ነው፡ ፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሲያበቃ እና በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በተሰጠ ማበረታቻ፣ በርካታ አዳዲስ እና ተመላሽ ዳያስፖራ ሚዲያዎች በአገሪቱ መመዝገብ እና መሥራት ችለዋል።

<u>ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት</u>፡- በአስቸኳይ አዋጁ ውስጥ በርካታ ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትን የሚገድቡ ክልከላዎች ተቀምጠዋል። እነርሱም አንዳንድ ገለልተኛ ድምጾች በጊዜያዊነት እንዲታፈኑ ሆኗል። ደንቦቹ በሰፊው ሲተረጎሙ በስውር ወይም በገሃድ አለመረጋጋትን ወይም ረብሻን ሊያስከትሉ የሚችሉ መልዕክቶችን ማስተላለፍን ይከለክላሉ። ገደብ ከተጣለባቸው ተግባራት መካከል ከማናቸውም የሽብር ወይም ጸረ ሰላም ኃይሎች ጋር ግንኙነት ማድረግን ይከለክላል፤ የሽብረተኛ ቡድኖችን ጽሑፎችና ዓርማዎች ማከማቸት፣ ማሰራጨት፣ በኃይማኖት ትምህርቶች ውስጥ የሚያነሳሱ መልዕክቶችን ማካተት፣ ፍርሐትን እና ግጭትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ትምህርቶች በኃይማኖት ተቋማት ውስጥ ማስተማር እንዲሁም በማንነት ወይም በብሔር ላይ የተመሰረተ ጥቃት ሊያስከትል የሚችል ንግግር ማድረግ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የታገዱ ነበሩ።

በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በማናቸውም መልኩ በግልጽ እና ሕዝብን ለኃይል ድርጊት ሊያነሳሳ የሚችል ተግባር መፈጸም፣ ለምሳሌ ጽሑፎችን ማተም፣ ማዘጋጀት ወይም ማሰራጨት፤ ትረኢቶችን ማሳየት፣ በማናቸውም ዘዴ መልዕክቶችን ለሕዝብ ማስተላለፍ፣ ወይም ፈቃድ ሳይገኝ ማናቸውንም ሕትመት ከውጭ አገር ማስገባት ወይም ወደ ውጪ መላክ ክልክል ናቸው። ከዚህም ሌላ በዚህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አመጽን፣ ረብሻን ሊያስከትል፣ ጥርጣሬን ወይም በሰዎች ላይ ቅሬታን ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም መልዕክት በኢንተርኔት፣ በሞባይል ስልክ፣ በጽሁፍ፣ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ ማስተላለፍ በጥብቅ ተከልክሏል። ፖሊስ የዚህን መሰል ሚዲያ ባለቤት ወይም አሰራጭ ወደ ሆኑ ግለሰቦች ቤት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመግባት እንደ ምክንያት ተጠቅሞበታል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ብሔራዊ ሉዓላዊነትን በሚሸረሽር መልኩ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር የመረጃ ልውውጥ ማድረግን የሚከለክል ሲሆን፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትም ኢ-ሕገመንግሥታዊ በሆነ ሁኔታ ወይም ሉዓላዊነትንና ጸጥታን ይሸረሽራል ተብሎ በሚታሰብ መልኩ ለጋዜጠኞች መግለጫ ከመስጠት እንዲቆጠቡ ደንግጓል። በዚህ ሕግ ምክንያት ግለሰቦች ራሳቸውን ሳንሱር ያደርጋሉ ማለት ነው።

የተቃውሞዎች እና የለውጥ ጥያቄዎች ገፊ ምክንያት ኢሕአዴግ በማስፈራራት፣ ለምሳሌ ጋዜጠኞችን፣ በኢንተርኔት አማካኝነት ሂስ የሚጽፉ ሰዎችን እና የተቃውሞ ፓርቲ አባላትን ባልተቋረጠ ሁኔታ በማሰር ሂስን ለማፈን መሞከሩ ነው። በተጨማሪም መንግስት የተቃዋሚ ፖለቲካ አካላትን እንቅስቃሴዎች ይቆጣጠር እና ጣልቃ ይገባ ነበር። አንዳንድ ዜጎች በጸጥታ ኃይሎች የሚያደርሱባቸውን ጥቃት ቢገልጹ መንግሥት የበቀል እርምጃ ይውስድብናል የሚል ስጋት ነበራቸው። የሐሰት አሉባልታ በማሰራጨት ሕዝቡን ከማነሳሳት ጋር በተያያዘ በዚህ ሕግ

ሥር በመንግሥት ላይ ሂስ የሚያቀርቡ በግል ወይም በይፋ ለሕዝቡ መግለጫ የሰጡ ሰዎችን በቁጥጥር ስር በማዋል አስሯል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ወደ ሥልጣን ሲመጡ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ለአገሪቱ መጪ ጊዜ እጅግ ተፈላጊ ነው ብለዋል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አከታትለው እንደገለጹት መንግሥት ላይ ሂስ የሚያቀርቡ ሰዎችን በቁጥጥር ስር ማዋል፣ ማሰር፣ ጥቃት ማድረስ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሶአል።

<u>የፕሬስ እና ሚዲያ ነጻነት</u>፡- ገለልተኛ ጋዜጠኞች በግላቸው በተመጣጣኝ ዋጋ ገለልተኛ ማተሚያ ቤት ለማግኘት ያላቸው ዕድል በአንድ በመንግሥት ባለቤትነት ስር ባለ ማተሚያ ድርጅት የተገደበ ነው። በዚህም ረገድ መንግሥት ያስፈራራል። ቢያንስ አንድ የመገናኛ አካል ከውጭ አገር የማተሚያ መሳሪያ ከውጭ አገር ለማስመጣት ሙከራ አድርጎ ነበር፤ ነገር ግን በስራ ላይ ለማዋል ፈቃድ ለማግኘት ሳይችል ቀርቷል። ገለልተኛ የዜና ማሰራጫዎች እንዳሉት የሕትመት ሚዲያ ቁጥር ማነስ፣ ዝቅተኛ ስርጭት እና የሕትመት መዛባት ዋነኛ ምክንያት የማተሚያ ተቋም እጥረት መሆኑን ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ስድስት ገለልተኛ ጋዜጦች በድምሩ በሳምንት የ43,000 ቅጂዎች ስርጭት ነበራቸው፤ በተጨማሪ ሁለት በስፖርት ላይ ያተኮሩ ጋዜጦች ነበሩ። ከዋና ከተማዋ ውጪ ገለልተኛ ጋዜጦች አልነበሩም። በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተሙ ስምንት ገለልተኛ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ ጋዜጦች እና በወር ሁለት ጊዜ የሚታተሙ መጽሄቶች በድምሩ የ28,000 ቅጂዎች ስርጭት ነበራቸው። በመንግሥት ባለቤትነት ስርያሉ ጋዜጦች ደግሞ በድምሩ በቀን የ50,000 ቅጂ ስርጭት ነበራቸው። አብዛኞቹ ጋዜጦች የሚታተሙት በሳምንት ወይም በሁለት ሳምንት ጊዜ ሲሆን፣ በመንግሥት የሚታተሙ ጋዜጦች እና አንድ *ዴይሊ ሞኒተር* የተባለ የግል ጋዜጣ ደግሞ ዕለታዊ ነበሩ። በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉ ሚዲያዎች የመንግሥትን እና የገዢውን ፓርቲ የኢሕአዴግን አቋሞች በቅርበት ያንጸባርቃሉ። በብሔራዊ ደረጃ ስርጭት ያለውን ቴሌቪዥን እና ሬዲዮ የሚቆጣጠረው መንግሥት ሲሆን፣ እርሱም ለአብዛኛው የአገሪቱ ዜጋ ብቸኛው የዜና ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። መላውን አገሪቱን የሚሸፍኑ ሁለት የመንግሥት የሬዲዮ ጣቢያዎች ያሉ ሲሆን፣ ሰባት FM ሬዲዮ ጣቢያዎች በዋና ከተማዋ ውስጥ ያሰራጫሉ፤ በትግራይ ክልል አንድ FM ሬዲዮ እና በሌሎች ክልሎች ደግሞ 28 የማኅበረሰብ ሬዲዮ ተቋማት ያሰራጫሉ። የመንግሥት አካል የሆነው የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በአገሪቱ ከፍተኛ ስርጭት ያለው ሲሆን፣ ከእርሱ በመቀጠል ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሰፊ የስርጭት ሽፋን አለው፤ ፋና የገዢው ፓርቲ መገናኛ ብዙሃን

ነው ይባላል። የኢትዮጵያ ብሮድካስት ሰርቪስን አካትቶ የተወሰኑ በሳተላይት ላይ የተመሰረቱ የግል የቴሌቪዥን ጣቢያዎች አሉ።

የፖለቲካ እና የኃይማኖት ድርጅቶች እንዲሁም የውጭ አገር ዜጎች የብሮድካስት ጣቢያዎች ባለቤቶች እንዲሆኑ ሕጉ አይፈቅድም።

ሁከት እና ማሳደድ፡- መንግሥት በጋዜጠኞች ላይ ይፈጽም የነበረው በቁጥጥር ስር የማዋል ተግባር፣ ጥቃት እና ክስ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰ ሲሆን፣ በቁጥጥር ስር ውለው የነበሩ ጋዜጠኞች ተለቅቀዋል። ከኤፕሪል (ከሚያዝያ) ጀምሮ፣ ታዋቂ በሆነ ጋዜጠኛ ላይ የደረሰ እስራት የለም። በጃንዋሪ 9 እና 10 (ጥር 1 እና 2) ፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር 14 የእስልምና አክቲቪስቶችን እና ጋዜጠኞችን፣ ለምሳሌ ዳርሰማ ዶሪን እና ኻሊድ መሐመድን ከእስር ነጻ አድርጓል። የእስረኞች መፈታት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዲሴምበር 2017 (ታህሳስ 2010) የጸረ ሽብር ሕጉን በመተላለፍ በተከሰሾች ላይ አስተላልፎ የነበረውን ውሳኔ ተከትሎ ነበር።

በሳንሱር እና በይዘት ላይ ስለሚደረግ ገደብ፡- በርካታ የግል ጋዜጦች በመንግሥት መደበኛ ያልሆነ ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው ገልጸዋል። መንግሥት ከሚያደርጋቸው ጣልቃ ገብነቶች መካከል እንደ ምሳሌ የሚጠቀሰው አንዳንድ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና ለመንግስት ወሳኝ ናቸው በሚባሉ አርዕስትን አስመልክቶ ከመንግሥት ባለሥልጣናት የስልክ ጥሪ መደረጉ በዚህ ስር የሚካተቱ ናቸው። የግሉ ዘርፍ እና የመንግሥት ጋዜጠኞች በየእለቱ ራሳቸውን ሳንሱር ያደርጋሉ። ብዙ የአገር ውስጥ እና የውጭ ጋዜጠኞች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት ራስን ሳንሱር ማድረግ መጨመሩን ገልጸዋል።

ብሔራዊ ጸጥታ፡- በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ስር ማለትም ከፌብርዋሪ 15 (የካቲት 8) እስከ ጁን 5 (ግ ንቦት 28) መንግሥት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ህግጋት ሂስን ለማፈን ተጠቅሞባቸዋል። ጁላይ 5 (ሰኔ 28) ቀን ፣ ፓርላማው የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን (OLF)፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባርን (ONLF) እና ግንቦት 7ን ከሽብርተኞች ዝርዝር በህግ ሰርዟል። ከስረዛው በኋላ የግል እና የመንግሥት ጋዜጠኞች ስለእነርሱ መዘገብ እጅግም አላስፈራቸውም።

መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ላይ የተከተለ ውጤት፡- ጁላይ 13 (ሐምሌ 6) ቀን በሚኤሶ ከተማ ማንነታቸው ያልታወቀ ወጣቶች ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በመጓዝ ላይ በነበረ የጋዜጠኞች ቡድን ላይ ጥቃት ሰነዘሩ። የጋዜጠኞቹ ዓላማ የኤርትራው ፕሬዚደንት በኢትዮጵያ ላደረጉት ጉብኝት ሽፋን መስጠት ነበር። ከቡድኑ አባላት መካከል አምስቱ በመንግሥት ባለቤትነት ስር ያለው የድሬዳዋ ማስ ሚዲያ ኤጀንሲ አባላት ነበሩ። ይጓዙበት

የነበረው መኪና ሹፌር ጁላይ 19 (ሐምሌ 12) በደረሰበት ጉዳት ምክንያት በሐረር ሆስፒታል ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ የፖለቲካ ውይይትን ለማመቻቸት እና ለማጎልበት የሰፊው ሪፎርም አካል በሆነ መልኩ የዳያስፖራ ሚዲያ አካላት ወደ አገሪቱ እንዲገቡ ጋበዙ። ዋና ዋና ሚዲያዎች እና ጦማርያን ወደ አገር ውስጥ ገብተው ያለምንም ችግር መስራት ጀምረዋል። የሚዲያ አካላት አሁን ያገኙትን የነጻነት ገደቦች ሲፈትሹ በጥንቃቄ ነበር። በርካታ የሕትመት ሚዲያዎች በሚገባ የመረመሯቸውን ችግሮች ያለምንም የአጸፋ ምላሾች ሲያጋልጡ ነበር።

## የኢንተርኔት ነጻነት

መንግስት በየጊዜው ኢንተርኔትን ሲያውክ እና ሲያቋርጥ ቆየቷል፤ የተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያ ድረ ገጾችም የተዘጉባቸው ወቅቶች ነበሩ። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተፈጻሚ በተደረገበት ጊዜ መንግሥት በፌብርዋሪ (በየካቲት) እና በኤፕሪል (በሚያዝያ) ከአዲስ አበባ ውጪ በተለይ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች ኢንተርኔትትን ዘግቶ ነበር ። ባለስልጣናት በኤፕሪል ወር የኢንተርኔት ግንኙነት እንዲቀጥል ያደረጉሲሆን፣ ከዚህ ቀደም በአገሪቱ ዝግ የነበሩ 260 ድረ ገጾችን ከፍተዋል። ከእነርሱም መካከል ጦማሮች፣ የግንቦት 7፣ የኦነግ እና የኦብነግ ድረ ገጾች፣ የዜና አውታሮች ለምሳሌ *አል ጀዚራ*፣ *ቢቢሲ* እና *ሪልክሊርፖለቲክስ* ይገኙባቸዋል። የመንግሥት ኃላፊዎች በሴፕቴምበር (በመስከረም) እና በኦክቶበር (በጥቅምት) በወቅቱ ለተፈጠረው አለመረጋጋት ምላሽ ለመስጠት በአዲስ አበባ ውስጥ እና በአካባቢው ተንቀሳቃሽ የኢንተርኔት ግንኙነት እንዳይኖር አደረጉ።

በኦገስት (በነሐሴ) ወር የመጀመሪያ ቀናት መንግሥት በአገሪቷ ምስራቅ ክፍል ማለትም በድሬዳዋ፣ ሐረር እና ጅግጅጋ በጊዜያዊነት የብሮድባንድ እና ኢንተርኔት አገልግሎቶችን ዘጋ ይኸውም የተደረገው ሁካታ በመፈጠሩ ነው። በሴፕቴምበር (በመስከረም) ወር ተቃውሞው ኃይል የተሞላበት ሲሆን ኢንተርኔት እና ሞባይል ዳታ አዲስ አበባ ውስጥ እንዲዘጉ ተደረገ። መንግሥት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን ሳይኖረው ግለሰቦች በኢንተርኔት የሚያደርጓቸውን ግንኙነቶች ይከታተላል የሚሉ ተዓማኒነት ያላቸው ስሞታዎች ቀርበዋል። በመንግስት የዞታ ስር ያለው ኢትዮ ቴሌኮም በአገሪቱ ውስጥ ብቸኛው የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ነበር።

በኮምፒውተር የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ሕጉ ከሚገባው በላይ ሰፊ የሆኑ ደንቦች ያሉት በመሆኑ፣ የመናገር እና የመጻፍ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ለማፈን ሊውሉ ይችላሉ። በዚህ ስር ለምሳሌ በኮምፒውተር ሲስተም አማካኝነት ማንኛውንም ረብሻን፣

አለመረጋጋትን ወይም በሰዎች መካከል ግጭትን ሊፈጥሩ የሚችሉ የጽሑፍ፣ የቪድዮ ወይም የድምፅ ወይም ሌላ ማናቸውም ዓይነት መረጃ ማስተላለፍን ይጨምራል። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በኢንተርኔት፣ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት፣ በሚሴጅ እና በማኅበራዊ ሚዲያ አማካኝነት አለመረጋጋትን ወይም ግጭትን ሊፈጥሩ የሚችሉ መረጃዎችን ማስተላለፍን ይከለክላል። በመንግስት ይዞታ ስር ያለው ኢትዮ ቴሌኮም በአገሪቱ ውስጥ ብቸኛው የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ነበር።

ተጠቃሚዎች ከመንግሥት ክትትል ውጪ ሆነው በኢንተርኔት እና በኢሜል ለመጠቀም የሚያስችላቸውን መዳረሻ ቨርቹዋል ፕራይቬት ኔትወርክ አገልግሎትን ሰጪዎቹ ላይ ዘጋባቸው። እንዲህ ያሉት የኢንተርኔት አጠቃቀም ክትትል በቁጥጥር ስር መዋልን ማስከተሉን የሚያሳዩ ማስረጃዎች አሉ።

በኢንተርናሽናል ቴሌኮሙኒኬሽን ዩኒየን መረጃ መሠረት፣ በ2017 (2009/2010) ከጠቅላላው ሕዝብ 18.6 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ነበር።

## አካዳሚያዊ ነጻነት እና ባሕላዊ ክስተቶች

መንግሥት አካዳሚያዊ ነጻነትን በቀዳሚነት ተቆጣጣሪ መምህራንን በማሰማራት እና በሥርዓተ ትምህርት አማካኝነት ገድቧል። ባለሥልጣናት በተደጋጋሚ በዩኒቨርሲቲ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የንግግር እና ሃሳብን የመግለጽ መብት ላይ ገደብ ይጥላሉ። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ደንቦች በትምህርት ተቋማት አመጽ ማድረግን የሚከለክሉ በመሆናቸው፣ የመንግሥት ኃለፊዎች ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር በአመጽ ላይ በሚሳተፍ ማንኛውም ተማሪ ወይም ሠራተኛ ላይ እርምጃ እንዲወስዱ የማዘዝን ስልጣን አላብሷቸው ነበር፤ እንዲሁም የሕግ አስከባሪ አካላት አምጽን እና ተቃውሞን ለመቆጣጠር ወደ ትምህርት ተቋማት ገብተው እርምጃ እንዲወስዱ ሥልጣን ሰጥቷቸው ነበር።

በተለያዩ ሪፖርቶች ላይ እንደተገለጸው፣ ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ፣ በትምህርተ ሚኒስቴር በኩል፣ ለገዢው ፓርቲ ድጋፍ ያላቸውን ተማሪዎች ለድህረ ምረቃ ዲግሪ እንዲመረጡ በማድረጉ ቀጠለበት። አንዳንድ የዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች የፓርቲ አባል የሆኑ ተማሪዎች ከምረቃ በኋላ በሁሉም መስኮች ቅድሚያ የቅጥር ዕድል እንዲያገኙ መደረጉን ተገንዝበዋል። የተለያዩ ተጨባጭ ሪፖርቶች እንዳሳዩት የኢሕአዴግ አባል ያልሆኑ መምህራን በቂ ዕድገት እና የሙያ ማሻሻያ ዕድል አያገኙም ነበር። በአካዳሚያዊ ሠራተኞች ላይ የሚወሰዱ ውሳኔዎች ላይ ግልጽነት ይጎድል ስለነበር ከፓርቲ ጋር ባለ ግንኙነት፣ በብሔር ወይም በኃይማኖት ላይ ተመስርቶ መድልዖ እንደሚደረግ አቤቱታ ይቀርብ ነበር።

ከተጠቀሱት ሌላ የትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ የግል ዩኒርሲቲዎች የሕግ እና የመምሕራን ትምህርት እንዳያስተምሩ ክልከላ ያደርጋል፡፡ ከዚህም ሌላ መመሪያው የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ሥርዓተ ትምህርታቸውን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሳይንስ እና ማኅበራዊ ሳይንስ የ70/30 ንጽጽር ጋር እንዲያጣጥሙ ያስገድዳል፡፡ በዚህም ምክንያት ማኅበራዊ ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት እየቀነሰ ሄዷል፤ በሌላ በኩል የግል ዩኒቨርሲቲዎች በይበልጥ ያተኮሩት በማኅበራዊ ሳይንስ ላይ ነበር፡፡

ሪፖርቶች እንደገለጹት የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ ተማሪዎች በሰላማዊ ሰልፍ ተሳትፈዋል በሚል ወይም ተቃዋሚዎች ናቸው በሚል ግንዛቤ ወይም በሁለቱም ምክንያት ክትትል እንዲደረግባቸው እና እንዲታሰሩ ተደርጓል፡፡ በሪፖርቶች መሠረት ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፎችን ከማድረጋቸው አስቀድሞ በኦሮሚያ በሚገኙ ዩነቨርሲቲ ቅጥር ግቢዎች የደንብ ልብስ እና ሲቪል የለበሱ የጸጥታ ኃይል አባላት በከፍተኛ ቁጥር እንዲጨምሩ ተደርጓል፡፡

## ለ. የሰላማዊ ስብሰባ እና የመደራጀት ነፃነት

መንግስት ቀደም ሲል በሰላማዊ ስብሰባ እና በመደራጀት መብት ላይ ገደቦች ጥሎ ነበር፡፡

### በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት

ህገ መንግስቱና ህጉ በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት መኖሩን ይደነግጋል፤ ይሁን እንጂ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (SOE) ደንቦች ከኮማንድ ፖስት፣ በአንዳንድ ሁኔታዎችም ከፌዴራል እና በሌሎች ሁኔታዎች ከተጨማሪ የአካባቢው አካላት ድጋፍ የሌላቸው ሰላማዊ ሰልፎችንና የአዳራሽ ስብሰባዎችን ከልክለዋል፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተነሳ በኋላ የደህንነት ሐይሎች ለተቃውሞዎች የሰጡት ምላሽ ይበልጥ እየለዘበ የመሄድ ምልክቶችን አሳይቷል፡፡ በጁላይ (በሐምሌ) እና በኦገስት (በነሐሴ) ወራት የፌዴራል ፖሊስና የአዲስ አበባ ፖሊስ በአዲስ አበባ ውስጥ ላሉ ባለስልጣናት የቅድሚያ ማስታወቂያ ባልተሰጠበት ሁኔታ ቢያንስ ለሶስት ትልልቅ ሰላማዊ ሰልፎች ጥበቃ አድርገዋል፡፡

ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በፊት ከሁለት ግለሰቦች የሚበልጡ የሕዝባዊ ስብሰባዎች ወይም የሰላማዊ ሰልፎች አደራጆች ከ48 ሰዓታት በፊት አስቀድመው ለመንግስት ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው፡፡ ባለስልጣናት ፈቃድ መስጠትን መከልከል ባይችሉም ለህዝብ ደህንነት ወይም ለመዘዋወር ነጻነት ሲባል ቦታው ወይም ጊዜው/ሰዓቱ እንዲለወጥ ማድረግ ችለዋል፡፡

አንድ ዝግጅት ወደ ሌላ ቦታ ወይም ጊዜ/ሰዓት እንዲለወጥ ባለስልጣናት ካሳሰቡ፣ በህጉ መሰረት ባለስልጣናቱ ጥያቄው በቀረበ በ12 ሰዓታት ውስጥ ለአዘጋጆቹ በጽሑፍ ማስታወቅ አለባቸው።

ኢሕአዲግ ለስብሰባዎችና ለዝግጅቶች በአዲስ አበባ፣ በክልል ከተማች፣ እና በመንግስት ድርጅቶች ውስጥ ያሉትን የራሱን የኮንፈረንስ ማዕከላት ተጠቅሟል። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ ባልተፈቀዱ ሰላማዊ ሰልፎች ወይም የአዳራሽ ስብሰባዎች ላይ የተደረገው ክልከላ በተለይ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ደንቦች ስር መደራጀትን አስመልከቶ በባለስልጣናት ማስፈራራት እንደደረሰባቸው ሪፖርት ላደረጉ የሲቪል ማህበረሰብና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የስብሰባዎችን ዝግጅት፤ የስልጠና ክፍለ ጊዜያትን እና ሌሎች ስብሰባዎችን በከባዱ ገድቧል።

## የመደራጀት ነጻነት

ህጉ የመደራጀት ነጻነትና ባልተገደበ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የመሰማራት መብትን ቢደነግግም፣ ይህንን መብት መንግስት በጥብቅ ገድቧል (ክፍል 3 እና 5 ይመልከቱ)፡ ፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁና ተጓዳኝ ደንቦቹ የሰራተኛ ድርጅቶች ለመንቀሳቀስ ያላቸውን ችሎታ ገድበዋል (ክፍል 5 ይመልከቱ)። ብሔራዊ ልዕልናን እና ደህንነትን በሚሸረሽር ሁኔታ ከውጭ መንግስት ወይም መያድ ጋር መረጃ መለዋወጥን ወይም ግንኙነት ማድረግን ደንቦቹ በመከልከላቸው፣ ይህ ሁኔታ በሐገር ውስጥና በዓለምአቀፍ ድርጅቶች መካከል ተግባቦትን ቀንሷል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህግ ተብሎ ጭምር የሚጠራው የበጎ አድራጎትና ማህበራት አዋጅ (CSP)፣ ለመያድና ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጡ ያልታወቁ ልግስናዎችን ከልክለዋል። በመሆኑም ስጦታ ማድረግ የሚችሉ ለጋሾች ሁሉ ስማቸው በመንግስት ሪኮርድ ላይ እንደሚሰፍር ተገንዝበው ነበር። በሰላማዊ የመሰብሰብ እና የመደራጀት ነጻነት መብቶች ላይ የተባበሩት መንግስታት ልዩ ራፖር አቅራቢ የ2013
(2005/2006) ሪፖርት፡- "የእነዚህ ድንጋጌዎች በስራ መዋል ግለሰቦች ማህበራትን በስኬት መስርተው ለማንቀሳቀስ ባላቸው ችሎታ ላይ አውዳሚ ተፅዕኖ አሳድሯል" ሲል ገልጾአል። ለምሳሌ ያህል በሐገሪቱ ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉ አለማቀፍ መያድ በውጭ ሐገራት ባሉ የሐገሪቱ ኤምባሲዎች በኩል ማመልከቻ አስገብተው ማምልከቻውን የውጭ ጉዳይ

ሚኒስቴር ለእሺታ ወደ መንግስት የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ ማቅረብ ነበረበት። ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በጠቅላይ አቃቤ ህግ ለሚመራው ሂደት ለውጥን ለማበረታታት የማስፈፀሚያ ዘዴ አድርጎ ከጸረ-ሽብር አዋጅ እና ከሚዲያ ህግ ጋር የበጎ አድራጎትና ማህበራትን አዋጅ ተሐድሶ ቅድሚያ ሰጥተዋል።

### ሐ. የሐይማኖት ነፃነት

በ WWW.state.gov/religiousfreedomreport/. ላይ የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ሐይማኖቶች ነጻነት ሪፖርት ይመልከቱ።

### መ. የዝውውር ነፃነት

ህጉ ለሀገር ውስጥ ዝውውር፣ ለውጭ ሐገር ጉዞ፣ ወደውም ተሰዶ ለመሄድ (emigration)፣ እና ከውጭ ለመመለስ የመቻልን ነፃነት ይደነግጋል። መንግስት በሐገር ውስጥ ለተፈናቀሉ ግለሰቦች፣ ለስደተኞች፣ ከስደት ተመላሾች ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ዜግነት አልባ ሰዎች እና አሳሳቢ ችግር ላለባቸው ሌሎች ግለሰቦች ከለላ እና እርዳታ በመስጠት ረገድ ከዩ.ኤን. የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR) መ/ቤት እና ከሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ትብብር አድርጓል። አንዳንድ ጊዜ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንደ ሐገሪቱ ጠረፎች በመሳሰሉ ለደህንነት ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች የመንቀሳቀስ ችሎታቸው በባለስልጣናት ወይም በታጠቁ ቡድኖች ተገድቧል።

<u>የሐገር ውስጥ እንቅስቃሴ/ዝውውር፡-</u> በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መሰረት አንዳንድ የሀገሪቱ ክልሎችና ደንበሮች ተከልክለው ነበር። አዋጁ ካበቃ በኋላ ክልከላዎቹ ቆመዋል።

<u>የውጭ ሐገር ጉዞ፡-</u> ሙያዊ እውቀት የሌላቸው ሰራተኞች ለስራ ቅጥር ወደ መካከለኛ ምስራቅ በሚያደርጉት ጉዞ ላይ መንግስት በ2013 (2005/2006) ያስቀመጠው ክልከላ ፀንቶ ቆይቷል። ክልከላው ለኢንቨስትመንት ወይም ለሌሎች የንግድ ስራ ምክንያቶች በሚጓዙ ዜጎች ላይ ተፅዕኖ አላሳደረም። መንግስት ክልከላውን ያወጀው በውጭ ሐገር በተለይም በመካከለኛ ምስራቅ በቤት ሰራተኞች ላይ የሚደርሰውን ትንኮሳ፣ ማስፈራራትና ስቃይ ለማገድ መሆኑን ገልፆአል።

<u>በፖለቲካ ምንክንያት በግዴታ ከሀገር ውጭ የመኖር ሁኔታ፡-</u> የጠቅላይ ሚኒስቲሩ የእርቅ ጥሪ፣ ፓርላማው ከሽብርተኛ ዝርዝሮች ላይ ቡድኖችን ማውጣቱ እንዲሁም የምህረት አዋጅ

መታወጁ በስደት የነበሩ ብዙ ተቃዋሚ ቡድኖች፣ የፖለቲካ አቀንቃኞች፣ ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ወደ ሐገር ተመልሰው በተሐድሶ ጥረቶች እንዲሳተፉ አበረታቷቸዋል።

## በሐገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች

በአለምአቀፍ የስደተኞች ድርጅት መግለጫ መሰረት በሚያዚያ ወር በደብብሕክ ጌዲኦ ዞን እና በኦሮሚያ ውስጥ በምዕራብ ጉጂ ዞን የተጀመሩት የብሔረሰብ ግጭቶች 970,000 ሰው እንዲፈናቀል አድርገዋል። በጌዲኦ ዞን የተፈናቃዩ ብዛት 820,000 የደረሰ ሲሆን፣ በምዕራብ ጉጂ ዞን 150,000 ሆኗል። በሐገሪቱ ሌሎች ክፍሎች ካሉ ነባር የመፈናቀል ሁኔታዎች ጋር ታክሎ የጌዲኦ-ጉጂ ግጭት ተከስቷል። በሜይ (ግንቦት) እና በጁን (ሰኔ) ወራት በሐገሪቱ ውስጥ 1,777,000 የተፈናቀሉ ሰዎች መኖራቸውን፣ ከነዚህም 1,205,000 የሚሆኑት በአብዛኛው በ2017 (2009/2010) በኦሮሚያ-ሱማሌ ግጭት መፈናቀላቸውን፣ እንዲሁም 536,000 በድርቅ እና በሌሎች ከአየር ንብረት በተያያዙ ምክንያቶች መፈናቀላቸውን አለማአቀፉ የስደተኞች ድርጅት አረጋግጧል።በኦሮሚያ እና በደብብሕ ክልሎች የድንበር አካባቢዎች እንዲሁም በኦሮሚያ እና በሶማሊ ክልሎች የድንበር ቦታዎች በዋናነት በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት 1,391,000 አዳዲስ የተፈናቀሉ ሰዎች ነበሩ።

አብዛኛዎቹ የውስጥ መፈናቀሎች ሰበባቸው ግጭት እንደሆነ በተለይም በመልካም አስተዳደር ጉድለትና በንብረት ክርክር ምክንያት በክልሎች እና በጎሳዎች መካከል የተከሰቱ ግጭቶች መሆናቸውን ባለስልጣናት ገልጸዋል። በሐገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ለአማራጭ የኑሮ መተዳደሪያ ለክህሎት ማጎልበቻ፣ ለካሳ ክፍያ እንዲሁም በስነ-ዜጋና ፖለቲካዊ ተግባር ለመሳተፍ እድላቸውን የሚወስን የሰነድ ማረጋገጫ የማግኘት መብቶቻቸው ብዙ ጊዜ ተገድበዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች መንግስት ለደህንነትና ለዘለቄታው በቂ ዝግጅቶች ሳይኖሩ ወደተፈናቀሉበት የሚመለሱ ሰዎችን አበክሮ አበረታትቷል። ሁለተኛ እና ሶስተኛ መፈናቀሎችን ባስከተለ ሁኔታ መንግስት ተመላሾችን ለመገፋፋት ምግብን መጠቀሙ ተዘግቧል።

## የስደተኞች ጥበቃ

ሐገሪቱ ከኤፕሪል (ሚያዝያ) ወር ጀምሮ ወደ 915,000 ስደተኞች አስተናግዳለች። ብዙ ስደተኞች የመጡባቸው ሐገራት ደቡብ ሱዳን (440,000)፣ ሶማሊያ (256,000)፣ ኤርትራ (168,000)፣ ሱዳን (44,000)፣ እና የመን (1800) ነበሩ።

ጥገኝነት የማግኘት እድል፡- ህጉ የጥገኝነት ወይም የስደተኝነት ደረጃ ለመስጠት የደነገገ ሲሆን፣ መንግስት ለስደተኞች አገልግሎት እና ጥበቃ ለመስጠት የስደተኝነት ደረጃ መወሰኛ ስርዓት ተጠቅሟል።

የሥራ ቅጥር፡- በዚህ ዓመት በኢትዮጵያ የሥደተኛ ደንብ መሰረት፣ መንግስት ለስደተኞች የስራ ፈቃድ አይሰጥም፣ ይህንን እና ሌሎች የስደተኛ መመሪያዎችን ለመለወጥ በ2019 (2011) መጀመሪያ ላይ ደንቡ ከወቅቱ ጋር ተሻሽሏል። መንግስት ራሳቸውን የሚችሉ እንደሆኑ ለታመነባቸው እና/ወይም በኢትዮጵያዊ ዜጋ ድጋፍ የሚደረግላቸው ስደተኞች ከካምፕ ውጭ የመኖር ፖሊሲን የደረገ ሲሆን ይህም አንዳንድ ስደተኞች ከካምፖች ውጭ በመኖር መደበኛ ባልሆኑ የኑሮ ገቢ ማስገኛ ዘርፎች እንዲሰማሩ አስችሏቸዋል።

ዘላቂ መፍትሔዎች፡- መንግስት ስደተኞችን በሐገሪቱ ውስጥ እንዲኖሩ ያስተናገደ ቢሆንም ለዜግነት የሚሆን መንገድ አልሰጠም ወይም ውህደት አላቀረበም። ተፈላጊዎችን ፈተናዎች ያለፉ ስደተኛ ተማሪዎች በመንግስትና በዩኤንኤችሲአር (ስደተኞች ጉዳይ ድርጅት) ክፍያ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን መከታተል ችለዋል።

ከስደት ተመላሾች፡- በዓመቱ ውስጥ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ስደተኞች ከሳውዲ አረቢያ ተመልሰው ሰበአዊ ትብብር አስፈላጓቸዋል። በዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት መግለጫ መሰረት እነዚህ ከስደት ተመላሾች በደረሱ ጊዜ በግብኣቶች እጥረት ምክንያት የተደረገላቸው ድጋፍ የተገደበ ነበር።

## ክፍል 3፡ በፖለቲካ ሂደት የመሳተፍ ነፃነት

ዜጎች በምስጢር የድምጽ መስጫ እንዲሁም በኣለምአቀፍና በተስተካከለ ምርጫ መሰረት በሚካሄዱ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫዎች መንግስታቸውን ለመመረጥ እንደሚችሉ ይደነግጋል። የገዢው ፓርቲ የምርጫ እድሎች ግን ይህንን ሁኔታ ገድበዋል።

### ምርጫዎችና ፖለቲካዊ ተሳትፎ

የቅርብ ጊዜ ምርጫዎች፡-ሐገሪቱ በ2015 (2007) የሐገሪቱ ፓርላማ አካል ለሆነው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብሔራዊ ምርጫዎች አካሄዳለች። በዚያው ዓመት ዘግየት ብሎ

ፓርላማው ጠቅላይ ሚኒስትር በማድረግ ኃ/ማሪያም ደሳለኝን በሙሉ ሃላፊነት መርጧል። ፌብሩዋሪ 14 (የካቲት 7) ኃ/ማሪያም ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን በፈቃዳቸው መልቀቃቸውን ያስታወቁ ሲሆን፣ በማርች 27 (መጋቢት 18) ኢሕአዲግ አብይ አህመድን የፓርቲው አዲስ ሊቀመንበር እና ለፌዴራል ጠቅላይ ሚኒስትርነት እጩ አድርጎ መርጧቸዋል። ከዚያም በተወካዮች ም/ቤት የድጋፍ ድምፅ ከተሰጠ በኋላ አብይ አህመድ በኤፕሪል 2 (መጋቢት 24) የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ስልጣን ይዘዋል።

በ2015 (2007) የብሔራዊ ፓርላማ ምርጫዎች ኢሕአዲግ እና ተባባሪ ፓርቲዎች ለፓርቲው ለአምስተኛ ጊዜ ተከታታይ የአምስት ዓመት የሥልጣን ዘመን በመስጠት ሁሉንም 547 መቀመጫዎች አሸንፈዋል። የመንግስት ክልከላዎች የድምጽ አሰጣጡን ገለልተኛ ታዛቢነት በከባዱ ገድበዋል። ምርጫዎቹን ለመታዘብ በብቸኝነት የተመረጠው አለምአቀፍ ድርጅት የአፍሪካ ሕብረት ብቻ ነበር። የሐገር ውስጥ ፖሊሶች ጣልቃ በመግባት፣ በመተናኮል እና ከፍ/ቤት ትዕዛዝ ውጭ በማሰር በተቃዋሚ ፓርቲ ታዛቢዎች ተከሰዋል። ከምርጫዎቹ በፊት ስድስት ዙር የሚዲያ ክርክሮች የተደረጉ ሲሆን፣ የውስጥ ሚዲያ ባጠቃላይ ክርክሮቹን በሙሉ ሲያስተላልፍ በጥቂቱ ብቻ ኤዲት ተደርገዋል። ክርክሮቹ ለምርጫው የሚወዳደሩ ትላልቅ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሁሉ አካተዋል።

ገለልተኛ ጋዜጠኞች ምርጫውን ሲዘግቡ መጠነኛ ችግር እንዳጋጠማቸው ገልጸዋል። አንዳንድ ገለልተኛ ጋዜጠኞች ተገቢና ወቅታዊ ማመልከቻዎች ካቀረቡ በኋላ ከምርጫው አንድ ቀን በፊት የታዛቢነት ሹመት እንደተቀበሉ ሪፖርት አድርገዋል። ከ2005 (1997)አጨቃጫቂው የብሔራዊ ምርጫ አንስቶ የተተገበሩ በርካታ ህጎች፣ ደንቦችና የአሰራር ስርዓቶች በምርጫው ሂደት ሁሉ ለኢሕአዲግ በግልጽ ያዘነበለ እድል ፈጥረዋል። ተቃዋሚ እጩዎችንና ደጋፊዎችን ማስፈራራት ጨምሮ ተገቢ ያልሆኑ የመንግስት ታክቲኮች ሪፖርት ተደርገዋል። ከምርጫዎቹ በፊትና ይህንኑ ወዲያው ተከትሎ ባለው ወቅት ቢያንስ ስድስት ከምርጫ ጋር የተያያዙ የሞት አደጋዎች መከሰታቸውን የተለያዩ ሪፖርቶች ገልፀዋል። ለመራጮች ትምህርት ለመስጠት ብቸኛ ሃላፊነት ያለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ (NEBE) ሲሆን፣ ለመራጮች ስለሚሰጥ ትምህርት በብዙ የሐገር ውስጥ ቋንቋዎች የሬዲዮ ፕሮግራሞችን እና የመምሪያ መፅሐፎችን (ማኑዋሎችን) አሰራጭቷል።

በቅድመ ምርጫ የዳሰሳ ጥናት የአፍሪካ ሕብረት የ2015 (2007)ቱን ምርጫዎች “የተረጋጉ፣ ሰላማዊና ተዓማኒነት ያላቸው” ሲል በመጥራት መንግስት ላደረጋቸው የምዝገባ ጥረቶች አድናቆቱን ገልጿል። ይሁን እንጂ ምርጫው ያጠነጠነበትን ህጋዊ ማዕቀፍ አስመልክቶ አሳሳቢ ያላቸውን ነጥቦች አንስቷል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ከ35 ሚሊዮን በላይ

መራጮችን የመዘገበ ሲሆን ማናቸውንም ፍትሐዊ ያልሆኑ የድምጽ ሰጪዎች ምዝገባ አጋጣሚዎችን አልዘገበም።

በሐገሪቱ ውስጥ ባለው ብጥብጥ ምክንያት ለግንቦት ወር ፕሮግራም የተያዘላቸውን የአካባቢ ምርጫዎች ፓርላማው ኤፕሪል 12 (ሚያዝያ 4) ቀን ለማስተላለፍ ወሰነ።
<u>የፖለቲካ ፓርቲዎችና ፖለቲካዊ ተሳትፎ፡-</u> በኢሕአዲግ ቁጥጥር ስር ያለው መንግስት በትጥቅ ትግል ላይ ያሉትን ጨምሮ ተቀማጭነታቸው በውጭ ሐገር የሆኑ ተቃዋሚ ቡድኖች ተመልሰው ከነውጥ የጸዳ ትግል እንዲያካሂዱ ጥሪ አቀረበ። በተግባራዊ ሁኔታ ኦነግን፣ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባርን፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባርን እና አግ7ን ጨምሮ ሁሉም ትልልቅ ተቃዋሚ ቡድኖች ጥያቄውን ተቀብለው ወደ ሐገሪቱ ተመለሱ።

ባለስልጣናት ከመጋቢት ወር 2009 ጀምሮ ከሽብርተኝነት ጋር በተዛመዱ ክሶች አስረውት የነበረውን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ የቀድሞ መሪን ማሙሸት አማረን የካቲት 7 ቀን ከእስር ፈቱ።

የኢሕአዲግ አባል ፓርቲዎች ለአባላቶቻቸው እድሎች ሰጡ፤ ፓርቲው ብዙ የንግድ ድርጅቶችን በቀጥታ በባለቤትነት በመያዝ ለታማኝ ደጋፊዎቹ ስራዎችና የንግድ ስራ እድሎችን ሰጠ። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያለችግር በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ቢሮዎችንና አዳራሾችን መከራየታቸውን ገልፀዋል። ከገዢው ቅንጅት ጋር ተባባሪነት የሌላቸው ስራ አጥ መጣቶች ስራ ለማግኘት የሚያስፈልጓቸውን “የድጋፍ ደብዳቤዎች” ከአካባቢ መስተዳድሮች ለማግኘት የተቸገሩባቸው ጊዜያት እንደነበሩ ሪፖርት ተደርጓል።

የተመዘገቡ የፖለቲከ ፓርቲዎች የሐገር ውስጥ ቢሮዎችን ለመክፈትና ለመከራየት ከክልል መንግስታት ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ከ2020 ብሔራዊ ምርጫ አስቀድሞ በዓመቱ ውስጥ ብዙ ቢሮዎች ለመክፈት መቻሉን ቢያንስ አንድ ትልቅ ተቃዋሚ ፓርቲ ሪፖርት አድርጓል። “ህዝባዊ ስብሰባዎችን” ሪፖርት እንዲያደርጉና ለህዝብ የድጋፍ ሰልፎች ፈቃድ እንዲያገኙ የሚያስገድዱ ህጎች የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ገድበዋል።

<u>የሴቶችና የአናሳ ቡድኖች ተሳትፎ፡-</u>በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ ሴቶች በፖለቲካ ሕይወት እንዳይሳተፉ የሚገድቡ የአባታዊ ስርዓቶች ቢኖሩም ሴቶች ወይም አናሳ ቡድኖች ድምጽ ከመስጠት ወይም በፖለቲካ ሕይወት ከመሳተፍ የሚያግዳቸው ህግ የለም። መሻሻሎች ቢኖሩም ግን ሴቶች ለስራ መደቦች በመመረጥ እና በመሾም በጉልህ ሁኔታ ውክልናቸው አንሶ ቆይቷል።በኦክቶበር (በጥቅምት) ወር ጠቅላይ ሚኒስትሩ 10 የሴት ሚኒስትሮች

ያሉበትን አዲስ ካቢኔ፣ ወይም በተያዘው ካቢኔ ግማሽ እንደሆኑ አሳውቀዋል። በተጨማሪም በጥቅምት ወር ሳህለወርቅ ዘውዴ የሐገሪቱ የመጀመሪያ የሴት ፕሬዘዳንት ሆነዋል። የሳህለወርቅ ዘውዴ ሹመት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአስዳደራቸው ውስጥ የሴቶችን አቅም ለማጎልበት ከገለፁት ግብ ጋር የተጣጣመ ነበር። በሕዳር ወር ፓርላማው የሐገሪቱን የመጀመሪያ ሴት የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዘዳንት ቃለ መሐላ አስፈፀመ። በብሔራዊ ፓርላማ ውስጥ ሴቶች 38 በመቶ መቀመጫዎች፣ ማለትም ከ547 ውስጥ 211 ይዘዋል።

የመንግስት የብሔር ፌዴራሊዝም ፖሊሲ በፌዴሬሽን ም/ቤት (በላይኛው የፓርላማ ምክር ቤት) ለሁሉም ትልልቅ የብሔር ቡድኖች ውክልና ለመስጠት የግለሰብ/የተናጠል መራጭ ማህበረሰብ ምስረታን አስከትሏል። መንግስት ከ80 በላይ ለሆኑ ብሔረሰቦች እውቅና የሚሰጥ ሲሆን፣ ቢያንስ እያንዳንዱ አባል በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውስጥ እያንዳንዱን “ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ እና ህዝብ” እንደሚወክል ህገ መንግስቱ ይገልጻል።

## ክፍል 4፡ በመንግስት ውስጥ ሙስና እና የግልጽነት እጦት

ህጉ ለሙስና ጥፋት የወንጀል ቅጣቶችን ይደነግጋል። መንግስት ህጉን በተሳካና በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አላደረገም።

ሙስና፡- ሙስና በተለይም ጉቦ መጋበዝ ፖሊሶችንና የፍትሕ ሙስናን ጨምሮ በአዋኪነት ዘልቋል። የመንግስት ባለስልጣናት የመሬት ምደባ ሂደቱን እንደጠመዘዙና በመንግስት ወይም በፓርቲ ባለቤትነት ስር ያሉ የንግድ ድርጅቶች በግንባር ቦታ ላይ ለሚገኙ የመሬት ሊዞች እና ብድር አድሎአዊ እድል ማግኘታቸውን አንዳንድ ባለድርሻ አካላት ያምናሉ። ጠቅላይ አቃቤ ህግ የሙስና ክሶችን እንዲመረምርና ክስ እንዲመሰርት ህጉ ሃላፊነት ሰጥቶታል።

በጥር ወር 2017 (2010)፣ በዘዴ የተፈፀሙ የሙስና ክሶችን የመመርመር ስልጣን ያለው የሙስና ዳይሬክቶሬት በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ መቋቋሙን የቀድሞው ጠ/ሚር ኃ/ማሪያም አውጀዋል። መንግስት የምርመራ ቢሮውን የመሰረተበት ምክንያት በመንግስት ቢሮክራሲ ውስጥ ሁሉ ግልጽነትን ለማጎልበት ነው።

ሜይ 25 (ግንቦት 17) ቀን የጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ ክሶችን ውድቅ ማድረጉን ለፍ/ቤቶች በማሳወቅ የቀድሞውን የጉምሩክና ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር መላኩ ፈንታ እና ምክትሉን ገ/ዋህድ ወ/ጊወርጊስን እንዲሁም በሙስና የተከሰሱ ደርዘን ያህል ታዋቂ የቢዝነስ

ሰዎችና ኩባንያዎች እንዲለቀቁ ትዕዛዝ ሰጥቷል። የዚያኑ እለት የቀድሞውን የፋይናስና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር ዴኤታን ጨምሮ ጁን 20 (ሰኔ 13) ቀን 2017 (2009) በተጀመረው የሙስና ዘመቻ ታስረው የነበሩ 17 የመንግስት ባለስልጣናት ቡድን ክሳቸው ውድቅ ተደረገ፡ ፡

ሐብትን ስለማሳወቅ፡- ሁሉም የመንግስት ባለስልጣናትና ሰራተኞች ሐብታቸውንና የግል ንብረታቸውን እንዲያስመዘግቡ ህጉ ያስገድዳል። ህጉ ደንብን በማያካብሩ ላይ የገንዘብና የወንጀል ቅጣትን ያካትታል። የፌዴራል የስነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን የፋይናንስ ማሳወቂያ ሪከርዶችን ይይዛል። በህጉ መሰረት እነዚህን ሪከርዶች ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የጽሑፍ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፤ የማሳወቅ ተግባር አስፈላጊነቱ በኮሚሽኑ ካልታመነበት በስተቀር የቤተሰብ ሐብት መረጃዎችን ማግኘት ሊገደብ ይችላል።

## ክፍል 5፡ ተፈፀሙ በተባሉ የሰብዓዊ መብቶች ላይ አለምአቀፋዊና መንግስታዊ ያልሆነ ምርመራን በተመለከተ መንግስት ያለው አመለካከት

በዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ወቅት በነበሩ ጉልህ የመንግስት ክልከላዎች ምክንያት በጣም ጥቂት የሐገር ውስጥ የሰብዓዊ መብት ቡድኖች ነበሩ የሚንቀሳቀሱት። ብቸኛው የሐገር ውስጥ፣ ገለልተኛ የሰብዓዊ መብቶች ቡድን የግብዓት-ተግዳሮት የገጠመው ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን (HRCO) ነው። በአባልነት ላይ የተመሰረተ፣ ወገናዊ ያልሆነ፣ መንግስታዊ ያልሆነ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ አካል ነው። ከተመሰረተ ጀምሮ ከመቶ ሪፖርቶች በላይ ያወጣው የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ብቸኛው መንግስታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተቆጣጣሪና ሪፖርት አቅራቢ ቡድን ሆኖ ቆይቷል። በዓመቱ ወቅት ያቀረባቸው ሪፖርቶች በብሔር የተነሳሱ ጥቃቶችን፣ ግጭቶችንና መፈናቀሎችን በሰነድ ማስረጃነት ይዟል። በአጠቃላይ መንግስት በሐገር ውስጥና በዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቡድኖችና ታዛቢዎች ላይ እምነት ማጣትና የተሰላቸ ቢሆንም ያ አመለካከትና እምነት ማጣት እየተለወጠ ይታያል። በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ ሚዲያዎች እንደ ሂውማን ራይትስ ዎች የመሳሰሉ ዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብት ቡድኖችን ይተቻሉ። ኦገስት 16 (ነሐሴ 10) ቀን፣ አራት የሐገር ውስጥ የበጎ አድራጎቶች እና የመብት ድርጅቶች፣ ለሰብዓዊ መብት ቡድኖች ጥብቅና በመቆም እና የመብት ተቆርቆሪ ቡድኖች እንዲንቀሳቀሱ ሰፊ ምህዳር በመስጠት ላይ ያተኮረ የኢትዮጵያ መብቶች ድርጅቶች ኮንሶርቲየም የሚባል አዲስ የመብቶች ቡድን ጀምረዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (CSO)፣ ከ10% በላይ የገንዘብ ድጋፋቸውን ከውጭ ምንጮች የሚያገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመጠነ-ሰፊ የስራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዳይሰማሩ ከልክሏል። ክልከላ የተደረገባቸው እንቅስቃሴዎች የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ወይም የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ህዝቦች፣ የጾታና ሐይማኖት እኩልነትን ማራመድ፣ የሕፃናትና የአካል ጉድለት ያለባቸውን ሰዎች መብት፣ የግጭት አፈታት ወይም እርቅ፣ የፍትሕና የህግ ማስከበር አገልግሎቶችን ብቃት ያካትታሉ። ህጉ የሲቪል ማህበረሰብ ስለ መልካም አስተዳደር፣ ሰብዓዊ መብቶች፣ ሙስና እና ግልጽነት ጥያቄዎችን የማንሳት አቅሙን በከባድ ሁኔታ ያግደዋል። የሐገር ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) የጥብቅና/የተቆርቋሪነት ስራቸውን ማቆም (በዚህም ከ10 በመቶ ገደብ በላይ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት መቻል) ወይም ለዚህ ክልከላ ተገዢ ባልሆነ ሌላ የትኩረት መስክ ላይ መመዝገብ አለባቸው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህግ ይህንን ድንጋጌ ያስቀረላቸው ጥቂት መያድ ነበሩ።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አጃቢ ደንቦች የመያድን የመንቀሳቀስ ችሎታ አግደዋል። ከኮሙኒኬሽንና ከመቻቻል ብሎም ህብረትን ከሸረሸሩ ተግባራት ጋር የተያያዙ ክልከላዎች በሪፖርቶችና በህዝብ መግለጫዎች ላይ ሰፊ ግለ-ሳንሱር አስከትለዋል። ባልተፈቀዱ የከተማ አዳራሽ ስብሰባዎች ላይ የተደረገ ክልከላ የስብሰባዎችን ዝግጅት፣ የሥልጠና ትምህርቶችንና ሌሎች ስብሰባዎችን ገድበዋል። ሁሉም ድርጅቶች በህግ አስከባሪ ባለስልጣናት በሚጠየቁ ጊዜ መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው መሆኑ የመረጃዎችን ምስጢራዊነት አስመልክቶ በርካታ አሳሳቢ ጉዳዮችን አስነስቷል።

አብዛኞቹ መያድ ወደ ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎችና ሌሎች የማሰሪያ ቦታዎች እንዳይደርሱ መንግስት ከልክሏል። መንግስት ታራሚዎችን እንዲጎበኝ የፈቀደለት ለጀስቲስ ፎር ኦል-ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ ሲሆን፣ ይህ ድርጅት ከውጭ ምንጮች ያልተገደበ የገንዘብ እርዳታ እንዲሰበስብና በሰብዓዊ መብቶች ጥብቅና እንዲሰማራ የሚያስችለው ከግዴታ ነፃ የሆነ መብት ነበረው። አንዳንድ ሌሎች መያድ የታራሚዎችን ምህረት የማግኘት እድል በማሻሻል ረገድ አዎንታዊ ሚና ተጫውተዋል።

የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፣ ሚዲያ፣ የበጎ አድራጎት ኤጀንሲዎችና የዲፕሎማቲክ ልዑኮች ወደ አንዳንድ አካባቢዎች እንዳይደርሱ በባለስልጣናት ተገድበዋል። መንግስት ወደ አስጊ አካባቢዎችና ክልሎች መያድ መግባት ስለሚያስችላቸው መብት ግልጽ መመሪያ ማጣቱን የቀጠለ ሲሆን፣ ይህም የክልል መንግስት ባለስልጣናት እና ወታደራዊ ባለስልጣናት የመያድን የመግቢያ መብት ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ወደ ፌዴራል መንግስት ባለስልጣናት

እንዲያስተላልፉ አድርጓል። ባለሥልጣናት ጋዜጠኞች ወደ አስጊ ክልሎች ከመግባታቸው በፊት እንዲመዘገቡ የጠየቁ ሲሆን በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ እንዳይገቡም ከልክለዋል። ለተወሰነ ወቅት የደህንነት ስጋቶችን እንደምክንያት በመጥቀስ የክልል ፖሊሶች ወይም የአካባቢው ሚሊሻዎች መያድ ወደ ልዩ አካባቢዎች እንዳይገቡ ስለማገዳቸው ሪፖርቶች ነበሩ።

<u>የመንግስት የሰብዓዊ መብት አካላት፡-</u> የእምባ ጠበቂ ቢሮ የማረሚያ ቤት ሁኔታዎችን መመርመር ጨምሮ በዋና የቅርንጫፍ ቢሮዎችና በባለስልጣናት የተፈፀሙ የብልሹ አስተዳደራዊ ተግባራትን ቅሬታዎች የመመርመር ስልጣን አለው። ከጁላይ 2017(ሐምሌ 2009) እስከ ሜይ (ግንቦት) ድረስ በ1360 ቅሬታዎች ላይ ምርመራዎች መጀመሩን ቢሮው ሪፖርት አድርጓል። በ717 ጉዳዮች ላይ አስፈጻሚ አካላት ደካማ የአስተዳደር ተግባራት መፈጸማቸውን ተቋሙ አረጋግጧል። በጣም ከባድ የሆኑት ብልሹ አሰራሮች መንግስት በአዲስ አበባ፣ በደብብህክ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በጋምቤላ ክልሎች ድጎማ ካደረገባቸው የመሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች እና የተጠቃሚ እቃዎች ህገ ወጥ ስርጭት ጋር የተያያዙ ናቸው፡ ፡

በተጨማሪም በቤቶች ልማትና ግንባታ እንዲሁም በመሬት አስተዳደርና በካሳ አከፋፈል ላይ ብልሹ አሰራር መኖሩን ተቋሙ ሪፖርት አድርጓል።

ተቋሙ አግባብነት ላላቸው ባለስልጣናት ግኝቶቹን ከማሳሰቢያዎች ጋር በማቅረብ ስለ ማሳሰቢያዎቹ አፈጻጸም ክትትል አድርጓል። አብዛኞቹ ኤጀንሲዎች ማሳሰቢያዎቹን አክብረው የማረሚያ እርምጃዎች የወሰዱ ሲሆን፣ 38 መ/ቤቶች በዚህ ረገድ ቸልተኛ ሆነው ተገኝተዋል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (EHRC) በሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ጥናት አካሂዶ በሶማሊያና ኦሮሚያ ግጭቶች ብሎም በኦሮሚያ ጉጂ ዞን እና በደብብህክ ጌዲዖ ዞን መካከል የተከሰቱትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መርምሯል። ኮሚሽኑ የእነዚህን ሪፖርቶች ግኝት ለህዝብ ግልጽ አላደረገም። ክልሉ በኦገስት 4 (ሐምሌ 28) በገጠመው ከባድ የሁከት ወቅት የወጣቶች ቡድንና የክልሉ የደህንነት ሐይሎች በሶማሊ ክልል ጅጅጋ በሚገኘው ቅርንጫፍ ቢሮው ላይ ጥቃት ማድረሳቸውን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ለሐገር ውስጥ ሚዲያ ሪፖርት አድርጓል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ሰራተኞች ቀጥተኛ ጥቃት ደርሶባቸው የአካባቢው ቢሯቸውም ተቃጥሏል። ኮሚሽኑ በአካባቢው በተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ላይ የነበሩትን የምርመራ ማስረጃዎች አጥቂዎቹ ለማጥፋት መሞከራቸውን ባለስልጣናቱ እንደሚያምኑ ተናግረዋል።

## ክፍል 6፡ መገለል፣ ማህበረሰባዊ የመብት ጥሰት እና ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር

የመንግስት ፖለቲካዊ ትራንስፎርሜሽን ከመንግስት ሐይሎች ጋር በሚደረግ ውጊያ የሞት ብዛትን ለመቀነስ አስተዋፅዖ ባደረገበት ሁኔታ፣ በማህበረሰቦችና በዜጎች መካከል የሁከት መጠን መጨመር ጀምሯል። ጁን (ሰኔ) ወር አጋማሽ ላይ፣ በኦፊሴላዊ መግለጫዎች መሰረት በደብብህክ ዋና ከተማ ሐዋሳ እና በደብብህክ ወላይታ ውስጥ የተከሰተው የብሔር ግጭት 15 ሰዎች እንዲሞቱ አድሯል። በጌዲዖ-ጉጂ አቅራቢያ ማህበረሰቦች መካከል የተከሰተው ነውጥ ወደ አንድ ሚሊዮን ሰዎች በማፋናቀል የሕግ አስከባሪዎች ሰላም ለማስፈን ካላቸው ችሎታ በላይ ሆኗል።

## ሴቶች

<u>አስገድዶ መድፈርና የቤት ውስጥ ጥቃት፡</u>- ህጉ አስገድዶ መድፈርን ወንጀል በማድረግ በጉዳዩ ከባድነት ላይ በመመስረት ከአምስት እስከ 20 ዓመት የሥር ቅጣት ይደነግጋል። ህጉ በትዳር ጓደኛ ለሚፈፀም የአስገድዶ መድፈር ጉዳይ በግልጽ መፍትሔ አይሰጥም። መንግስት ህጉን ሙሉ በሙሉ አላስከበረም። የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 564 በትዳር ጓደኛ የሚፈፀም አስገድዶ መድፈርን በልዩ ሁኔታ ሳይገልጽ በትዳር ጓደኛ ወይም በደንበ-ወጥ ህብረት አብሮ በሚኖር ግለሰብ ላይ የሚፈፀምን ጥቃት በአጠቃላይ ይሸፍናል። አንዳንድ ዳኞች ይህ አንቀፅ በትዳር ጓደኛ የሚፈፀሙ የአስገድዶ መድፈር ጉዳዮችን እንደሚዳስስ ቢተረጉሙም ሌሎቹ ግን እንዲህ አይነት ጉዳዮችን ችላ ብለው ያልፋሉ።

የቤት ውስጥ ጥቃት ህገ ወጥ ቢሆንም የመንግስት ህጎችን ማስከበር ወጥነት የለውም። በትዳር ጓደኛ የሚፈጸምን ጥቃት ጨምሮ የቤት ውስጥ ጥቃት የተስፋፋ ማህበራዊ ችግር ነው። በ2016 (2008/2009) የስነ-ህዝብ ስብጥር እና የጤና ቅኝት ጥናት (DHS) መሰረት 34 በመቶ ያገቡ ሴቶችና ከ15 እስከ 49 ዓመት ያሉ ሴቶች በትዳር ጓደኛ የሚፈፀም አካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም ስሜታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል። በደረሰው የጉዳት ክብደት ላይ በመመስረት ከአነስተኛ የገንዘብ ቅጣቶች እስከ 15 ዓመታት እስራት ይፈረዳል።

<u>የሴት ብልት መግረዝ/መቁረጥ (FGM/C):-</u> የ2016 (2008/2009) የስነ-ህዝብ ስብጥር እና የጤና ቅኝት ጥናት 65 በመቶ ልጃገረዶችና ከ15 - 49 ዓመት የሆኑ ሴቶች መገረዛቸውን አመልክቷል። የሴት ልጅ ግርዛት የመስፋፋት መጠን በሶማሊ ክልል (99 በመቶ) ከፍተኛ ሲሆን በትግራይ ክልል (23 በመቶ) አነስተኛ ሆኗል። የሴት ልጅ ግርዛት/የብልት አካል መቁረጥ ህገ ወጥ ሲሆን በወንጀሉ ሁኔታ ላይ በመመስረት እስርንና መቀጫን የሚያካትት ቅጣት አለው፡

፡ መንግስት ይህንን ክልከላ በንቃት አላስከበረም። በከተሞች አካባቢ ልማዱ አነስተኛ ነው። ቂንጥር የመቁረጥ ልማድ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ በወንጀል የሚያስጠይቅ ሲሆን በጉዳት አድራሾቹ ላይ የሶስት ወራት እስር ወይም ቢያንስ የ500 ብር (18 ዶላር) መቀጫ ይደነግጋል። የሴት ልጅን የመራቢያ አካላት ቆርጦ መስፋት (በጣም ከባዱና አደገኛው የብልት ግርዘት/የመስፋት ተግባር) ከአምስት እስከ 10 ዓመት በእስር ያስቀጣል። በመንግስት ምንጮች መሰረት በሴት ልጅ ግርዛት/የመራቢያ አካል መቆራረጥ ላይ የወንጀል ክስ ያልነበረ ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ ህጉ ስለመተግበሩ ሚዲያዎች ሪፖርት አድርገዋል።

ለተጨማሪ መረጃዎች አባሪ "ሐ" ን ይመልከቱ።

<u>ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፡-</u> መንግስት ድርጊቱን ለማስቆም ሙከራዎች እያደረገ ሳለ በአንዳንድ ክልሎች የቀጠለ ቢሆንም በጠለፋ ጋብቻን መፈፀም ህገ ወጥ ነው። በግዴታ የወሲብ ግንኙነቶች መፈፀም በአብዛኛው ጋብቻዎች በጠለፋ እንዲደመደሙ የሚያደርግ ሲሆን ሴቶች ዘወትር በጠለፋ ወቅት አካላዊ መጎሳቆል ይደርስባቸዋል። የጠለፋ ተግባራት በቤተሰቦች፣ በማህበረሰቦች እና በጎሳ ቡድኖች መካከል ግጭቶችን ያስከትላሉ። አጥፊው ወገን ጠለፋ ፈጽሞ ተበዳይዋ አጥቂውን ለማግባት ከተስማማች ቅጣት አይደርስበትም።

<u>ወሲባዊ ትንኮሳ፡-</u> ወሲባዊ ትንኮሳ የተስፋፋ ነበር። የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ከ18 እስከ 24 ወራት እስር ቢያዝዝም፣ ባለስልጣናት ግን በአብዛኛው ህጉን አያስከብሩም።

<u>የህዝብ ብዛትን በመቆጣጠር ረገድ የሚኖር ግዳጅ፡-</u> በግዴታ ስለተፈፀመ የጽንስ ማስወረድ ወይም ያለ ውዴታ መካን ስለመደረግ ተግባር ሪፖርቶች አልነበሩም።

<u>መገለል፡-</u> ሴቶችን ማግለል የተስፋፋ ተግባር ነበር። 80 በመቶ ህዝብ እንደሚኖርባቸው በሚገመቱ የገጠር አካባቢዎች እጅግ የባሰ ነበር። ህጉ ባልን የቤተሰቡ ህጋዊ አባወራ እና ከ5 ዓመት በላይ ለሆኑ ልጆች ብቸኛ ሞግዚት አድርጎ ዕውቅና መስጠትን የመሳሰሉ አግላይ ደንቦችን ይዟል። ፍ/ቤቶች በአብዛኛው የቤት ውስጥ ጥቃትን በራሱ ፍቺ እንደሚያስገኝ ምክንያት አድርገው አይቆጥሩትም። የጋብቻ ዓመታት ብዛት፣ ያደጉ ልጆችን ቁጥር፣ እና የጋራ ንብረትን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ፣ ግንኙነቱ ከቆመ ህጉ የሶስት ወራት የገንዘብ ድጋፍ ብቻ እንዲያገኙ ለሴቶች መብት ይሰጣል። በጋብቻ ሳይተሳሰሩ ተፈቃቅዶ አብሮ መኖር የሚሰጠው እውቅና ውሱን ነበር። ያለ ህጋዊ ጋብቻ አብሮ የሚኖር ባል ለቤተሰቡ የገንዘብ እርዳታ የመስጠት ግዴታ የሌለበት በመሆኑ በዚህ ምክንያት ሴቶችና ህፃናት አንዳንዴ መከዳት

ይገጥማቸዋል። ባህላዊ ፍ/ቤቶች በኢኮኖሚና ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ልማዳዊን ህግ መተግበራቸውን ቀጥለዋል።

ሴቶች የመንግስት መሬት እንዲያገኙ ሁሉም የፌዴራልና የክልል የመሬት ህጎች መብት ይሰጣሉ። የውርስ ህጎችም ባል የሞተባቸው ሴቶች በጋብቻ ወቅት የተገኘን የጋራ ንብረት እንዲወርሱ ያስችላል፣ ይሁን እና የሁለቱም ድንጋጌዎች መከበር የተስተካከለ አይደለም።

ሴቶች ገቢ የሚያስገኝ የሥራ ቅጥር፣ ብድር እና ድርጅትን በባለቤትነት የመያዝ ወይም የማስተዳደር እድል የማግኘታቸው ሁኔታ በዝቅተኛ የትምህርት ስኬታቸው እና በባህላዊ አመለካከት የተገደበ ነው። ሴቶች እነዚህን ዋነኛ የኢኮኖሚ አቅም ማበልፀጊያ መሳሪያዎች ለማግኘት ያላቸውን እድል ለማጎልበት ያለሙ በርካታ የእርምጃ ሐሳቦች ነበሩ።

## ህጻናት ልጆች

የልደት ምዝገባ፡- የአንድ ህጻን ዜግነት የሚገኘው ከወላጆቹ ነው። ህጻናት ሲወለዱ እንዲመዘገቡ ህጉ ያዝዛል። በሆስፒታሎች ውስጥ የሚወለዱ ህጻናት ተመዝግበዋል፤ ከሆስፒታሎች ውጭ የሚወለዱት አብዛኛዎቹ አልተመዘገቡም። በተለይ በገጠር አካባቢዎች እጅግ በጣም አብላጫ ቁጥር ያላቸው ህጻናት የሚወለዱት በቤት ውስጥ ነበር። በዓመቱ ውስጥ መንግስት ህጻናትን አለማስመዝገብ ህዝባዊ አገልግሎቶችን የሚያሳጣ መሆኑን በማስታወቅ የልደት ምዝገባዎችን ለመጨመር በ2017 (2008/2009) ዘመቻ ቀጥሏል።

<u>ትምህርት፡-</u> ህጉ ትምህርትን የግዴታ አያደርገውም። የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ሁሉን አቀፍ እና ከክፍያ ነፃ ቢሆንም በተለይ በገጠር አካባቢዎች የሐገሪቱን ወጣቶች የሚያስተናግዱ በቂ ት/ቤቶች የሉም። የትምህርት ቤት አቅርቦቶች ወጪ ለብዙ ቤተሰቦች የማይታሰብ አዝማሚያ ያለው ነው። የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት የምዝገባ ምጣኔ የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ለወንድ ልጆች 90 በመቶ እና ለልጃገረዶች 84 በመቶ እንደሆኑ ነበር ያመለከቱት።

<u>ህጻናትን ማጎሳቆል፡-</u>የሕጻናት ጉስቁልና እና ጥቃት የተስፋፋ ነበር። እንጥል መቁረጥ፣ ጉሮሮ መቧጠጥ እና የወተት ጥርስ መንቀል በጣም ከተስፋፉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል ነበሩ። ፡ በህጻናት ላይ የወሲብ ጥቃት በመፈፀም ተግባር ላይ መንግስት ቅጣት መጨመሩን በአፍሪካ ቻይልድ ፖሊሲ ፎረም የሚታተመው የ2013 (2005/2006) የህጻናት ደህንነት አፍሪካዊ ሪፖርት አረጋግጧል። “ለህጻናት ደጋፊ የሆኑ” ችሎቶች በህጻናትና በሴቶች ላይ

የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ሰምተዋል። በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንና በእምባ ጠበቂ ቢሮ ውስጥ የሴቶችና የሕጻናት ጉዳዮች ኮሚሽነር ነበር።

ያለ ዕድሜ እና የግዴታ ጋብቻ፡- ህጉ ለሴቶችና ለወንድ ልጆች የጋብቻ እድሜ 18 ዓመት መሆኑን አስቀምጧል። ይሁን እንጂ ባለስልጣናት ይህንን ህግ በወጥነት የማያስከብሩ ሲሆን የገጠር ቤተሰቦችም አንዳንድ ጊዜ ድንጋጌው ስለመኖሩ ግንዛቤው የላቸውም አይገነዘቡም። መንግስት ያለ ዕድሜ ጋብቻ ላይ መፍትሔ ለመስጠት የነደፈው ስልት ወንጀለኞችን ከመቅጣት ይልቅ ትምህርት በመስጠትና በማስተረቅ ነበር ያተኮረው። ለተጨማሪ መረጃዎች አባሪ “ሐ” ን ይመልከቱ።

በህጻናት ላይ የሚፈፀም ወሲባዊ ብዝበዛ፡- ወሲብን በስምምነት ለመፈፀም የተቀመጠው አነስተኛ ህጋዊ የእድሜ መጠን 18 ዓመት ቢሆንም ባለስልጣናት ይህንን ህግ አላስከበሩም። ለአቅመ ሄዋን/አዳም ካልደረሱ ህጻናት ጋር የወሲብ ግንኙነት በሚፈፅም ላይ ህጉ ከሶስት እስከ 15 ዓመት እስር ይደነግጋል። ለአቅመ ሔዋን/አዳም ባልደረሱ ልጆች የሚፈፀሙ የወሲብ ግንኙነቶችን የሚያሳዩ የብልግና ፅሑፎችን በሚያዘዋውሩ ላይ ህጉ የአንድ ኣመት እስርና የ10,000 ብር (357 ዶላር) መቀጫ ይደነግጋል። ህገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ዕድሜያቸው 11 ዓመት የሆኑ ሴት ልጆችን በሴተኛ አዳሪ ቤቶች እንዲሰሩ ይመለምላሉ። ወጣት ልጃገረዶች ከገጠር ወደ ከተማ እንዲዘዋወሩ እየተደረጉ በሆቴሎች፣ በቡናቤቶች በመዝናኛ የሪዞርት ከተማዎች እና በገጠር የጭነት መኪና መናህርያዎች ላይ በሴተኛ አዳሪነት እንዲሰማሩ ተደርገው ይበዘበዛሉ።

ጨቅላ ህጻናትን መግደል ወይም የአካል ጉድለት ያለባቸውን ጨቅላ ህጻናት መግደል፡- የአካል ጉድለት ያለባቸውን ጨቅላ ህጻናት ጨምሮ በሐይማኖታዊ ስርዓት እና በባዕድ አምልኮ የተመሰረተ የጨቅላ ህጻናት ግድያ ራቅ ያሉ የጎሳ አካባቢዎች በተለይም በደቡብ ኦሞ የቀጠለ ተግባር ነው። የአካባቢው መንግስታት ይህን ልማድ እንዲያስቀሩ ማህበረሰቦችን ለማስተማር ጥረዋል።

ተፈናቃይ ልጆች፡- በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር የ2010 (2002/2003) ሪፖርት መሰረት ወደ 150ሺህ ልጆች በጎዳና ላይ ኖረዋል። ከነርሱ መሀከል 60ሺህ ያህሉ በዋና ከተማ ውስጥ ነበሩ። ወላጆች በሚያጋጥማቸው ህመም ወይም በቂ ባልሆነ የቤተሰብ ገቢ ምክንያት ቤተሰቦች ልጆችን መርዳት አለመቻላቸው ችግሩን እንዳባባሰ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ይገልጻል። ፈጣን የከተማ መስፋፋት፣ ህገ ወጥ የስራ ቅጥር ደላሎች፣ በከተሞች ውስጥ የተሻለ ኑሮ የማግኘት ከፍተኛ ተስፋ እና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት በችግሩ ላይ

ተጨማሪ እክል መፍጠራቸውን በ2014 (2006/2007) በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተደረገው ጥናት ያስገነዝባል። እነዚህ ልጆች አብዛኛውን ጊዜ ይለምናሉ፣ አንዳንዴ የወሮ በላ ቡድን አካል ይሆናሉ ወይም ህጋዊ ባልሆነ የስራ ዘርፍ ይሰማራሉ።

<u>በተቋም ውስጥ ያሉ ህጻናት፡-</u> በዩኒሴፍ በታተመው ስታቲስቲክስ መሰረት በ2012 (2004/2005) በሐገሪቱ ውስጥ 4.5 ሚሊዮን፣ ማለትም ከህዝቡ 4.9 በመቶ የሚሆኑ ወላጅ አልባ ልጆች እንደነበሩ ተገምቷል። እጅግ ብዙዎቹ ከዘመድ አዝማድ ጋር ኖረዋል። መንግስታዊና በግል የሚንቀሳቀሱ የወላጅ አልባ ህጻናት ማሳደጊያዎች ከመጠን በላይ የተጣበቡ ሲሆኑ ሁኔታዎችም ብዙውን ጊዜ ንጽህና የጎደላቸው ነበሩ። በተቋም ውስጥ ያሉ ልጆች በቂ የጤና እንክብካቤ አላገኙም።

<u>አለምአቀፍ የሕጻን ልጅ ጠለፋዎች/አፈናዎች</u>፡- ሐገሪቱ በአለምአቀፍ የህጻን ልጅ ጠለፋ ሲቪላዊ ገጽታዎች ላይ የ1980 (1972) የሄግ ስምምነት አባል አይደለችም። ፓርላማው ጃንዋሪ 9 (ታህሳስ 30) የቤተሰብ ህግ ሰፊ የማሻሻያ አካል በማድረግ በሐገራት መካከል የሚደረጉ ጉዲፈቻዎችን የሚያገድ ህግ አሳልፏል። በ[https://travel.state.gov/content/travel/en/International-Parental-Child Abduction/for-provides/legal-reports-and-date.html](https://travel.state.gov/content/travel/en/International-Parental-Child%20Abduction/for-provides/legal-reports-and-date.html). በአለምአቀፍ በወላጅ የሕፃናት ጠለፋ ላይ የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ዓመታዊ ሪፖርት ይመልከቱ።

## ፀረ-ሴማዊነት

የአይሁድ ማህበረሰብ ወደ 2000 ሰዎች እንደነበሩ ይገልፃል። ፀረ-ሴማዊ ድርጊቶች ስለመፈፀማቸው ሪፖርቶች አልነበሩም። የአዲስ አበባ የአይሁድ ማህበረሰብ እምነቱን ለመተግበር የመንግስት ከለላ እንዳለው ማመኑን ሪፖርት አድርጓል። ነገር ግን የተወሰነ ማህበረሰባዊ መገለል ገጥሞታል።

## የሰዎች ህገ-ወጥ ዝውውር

በ [WWW.state.gov/j/tip/rls/tiprpt/](WWW.state.gov/j/tip/rls/tiprpt/). ላይ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የሰዎች ህገ-ወጥ ዝውውር ሪፖርት ይመልከቱ።

## የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች

ህገ መንግስቱ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የእኩል መብቶች ሃላፊነት አይሰጥም። አካላዊ እና አእምሮአዊ ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በስራ ቅጥር ረገድ አድሎዎ እንዳይደረግባቸው ህጉ የሚከለክል ሲሆን፣ በህንጻ ውስጥ ላሉ አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲያገኙ መመሪያ ይሰጣል ’ \፤ ነገር ግን የአእምሮ ወይም የስሜት ህዋሳት አካል ጉዳቶችን በግልጽ አይጠቅስም። መስማት ለተሳናቸው ሰዎች መኪና መንዳት ህገ ወጥ ነው።

ህጉ በአካል ጉዳተኝነት ላይ የተመሰረተ የስራ ቅጥር አድሎን ይከለክላል። በተጨማሪም የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰራተኞች ተገቢ የሥራና የስልጠና ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማቴሪያሎችን የማቅረብ ሃላፊነት የአሰሪዎች እንደሆነ ይገልፃል። በተለይም ህጉ የአካል ጉዳተኝነት ባለባቸው ሴቶች ላይ ላለው ተጨማሪ ሸክም እውቅናን ይሰጣል። መንግስት ፣ ለምሳሌ ያህል መስማት ለተሳናቸው እና በደንብ የመስማት ችግር ላለባቸው የመንግስት ሰራተኞች አስተርጓሚዎችን በመመደብ እነዚህን ህጎች ለማስከበር የወሰዳቸው እርምጃዎች የተገደቡ ናቸው። የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒቴር እና የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን የአካል ጉድለት ላለባቸው ግለሰቦች የስራ ቅጥር ህጎችን የመተግበር ሃላፊነት ነበረባቸው።

ህጉ ምንም እንኳ የተደራሽነት ደረጃዎችን የሚወስኑ ልዩ ደንቦች ባይኖሩትም የአካል ጉድለት ላለባቸው ሰዎች የህንጻ ተደራሽነት እና የንጽህና ቤት አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲያገኙ ይፈቅዳል። ህንጻዎችና የንጽህና ቤት አገልግሎቶች አብዛኛውን ጊዜ በአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አልነበሩም። የአካል ጉድለት ላለባቸው ሰዎች የህንፃው የምድር ቤት ወለል (ግራውንድ ፍሎር) ላይ ምርጫ እንዲሰጡ የንብረት ባለቤቶች የሚታዘዙ ሲሆን፣ አብዛኛውን ይህንኑ ያደርጋሉ። በዩኤን የስነ-ህዝብ ፈንድ እና የስነ-ህዝብ ካውንስል ሪፖርት መሰረት የአካል ጉድለት ካለባቸው ሶስት ልጃገረዶች አንዷ ቢያንስ አንድ የወሲብ ትንኮሳ ይገጥማታል። በተጨማሪም በቤታቸውና በማህበረሰባቸው ውስጥ ስልታዊ እና ነውጥ የተሞላበት ጥቃት ይገጥማቸዋል፡ ፡ ብዙዎቹ ለየት ያሉ በመሆናቸው እንደሚነቅፉ እና በጥንቆላ መተት ስር ተደርገው ስለሚታዩ እንደሚፈሩ ሪፖርቱ ይገልፃል።

የአካል ጉዳት ያለባቸው ሴቶች በትምህርትና በስራ ቅጥር ተጨማሪ መጥፎ እድሎች ይገጥሟቸዋል። በ2010 (2002/2003) የስነ-ህዝብ ካውንስል የወጣት አዋቂዎች የቅኝት ጥናት መሰረት፣ የአካል ጉድለት ከሌለባቸው 48 በመቶ ልጃገረዶችና 55 በመቶ ወንድ ልጆች ጋር ሲነፃፀሩ በትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩት የአካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች 23 በመቶ ነበሩ። በተጨማሪም የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጃገረዶች የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ልጃገረዶች ይበልጥ አካላዊና ወሲባዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል።

በብሔራዊ ደረጃ መስማትና ማየት ለተሳናቸው ሰዎች በርካታ ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን፣ የአእምሮ(ኢንተሌክቹዋል) ጉዳት ላለባቸው ልጆችና ወጣቶች በርካታ የሥልጠና ማዕከላት አሉ። ከዘጠኙ የክልል መንግስታት ውስጥ በአምስቱ የሰው ሰራሽ ጥርስና የአጥንት ህክምና ማዕከላት ኔትወርክ አለ።

የሰራተኛ ሚኒስቴር ከአካል ጉዳት ጋር በተዛመዱ ችግሮች ላይ ሰርቷል። የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች በመርዳት ረገድ፣ በተለይም በተደራሽነትና በሙያ ስልጠና ላይ ያተኮሩ በርካታ የሐገር ውስጥ መያድን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ህግ አሰነካክለዋቸዋል።

የተደራሽነት ችግሮች ተሳትፎን አስቸጋሪ ማድረጋቸው ቢቀጥልም እንኳ ህጉ አካል ጉዳተኞች ድምጽ የመስጠት መብታቸውን ወይም በሌላ አኳኋን በስነ-ዜጋ ጉዳዮች መሳተፋቸውን አይከለክልም። አብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ሲሆኑ፣ እነዚህ ግለሰቦች እንዲሁም አረጋዊያን፣ ነፍሰጡር ሴቶች እና አጥቢ እናቶች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

## ብሔራዊ/ የዘር/የጎሳ አናሳ ማህበረሰቦች

ሐገሪቱ ከ80 በላይ የብሔር ቡድኖች ያላት ሲሆን፣ከህዝቡ ወደ 34 በመቶ የሚሆነው ኦሮሞ ትልቁ ብሔር ነው። የፌዴራሉ ስርዓት በኢሕአዲግ የመጀመሪያ የአገዛዝ ዘመን ወቅት ትልልቅ የብሔር ቡድን መስመሮችን ተከትሎ ድንበሮችን አስምሯል፣ የወቅቱንም ህገ መንግስት አርቅቋል። ገዢው ፓርቲ እና ከትልልቆቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ አንዱ በበርካታ ብሔሮች ቅንጅት ላይ የተመሰረቱ ፓርቲዎች ቢሆኑም አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀዳሚነት በብሔር ላይ የተዋቀሩ ናቸው።

ሴፕቴምበር 15 እና 16 (መስከረም 5 እና 6)፣ ኦሮሞዎች ናቸው የተባሉ ወጣቶች በቡራዩ፣ ከታ እና አዋሽ ሜዳ (ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ ባሉ የኦሮሚያ ከተሞች) ዜጎችን በማጥቃት በአብዛኛው የጋሞ ብሔር ተወላጆችን እና ከደብብሕ ክልል የመጡ ተዛማጅ የብሔር ቡድኖችን 27 ነዋሪዎች ገድለዋል። ፖሊስ በጥቃቱ ውስጥ የተሳተፉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር አውሏል። ሴፕቴምበር 17 (መስከረም 7) የአዲስ አበባ እና በደብብሕ ክልል የአርባ ምንጭ ነዋሪዎች የብሔር ጥቃቶችን በማውገዝ ትልልቅ ተቃውሞች አድርገዋል።

በአዲስ አበባ አንዳንድ ክፍሎች የተካሄዱ ተቃውሞዎች ወደ ሁከት ተለውጠው በደህንነት ሐይሎች እጅ የህይወት መጥፋትን አስከትሏል። የደህንነት ሐይሎች ጠብመንጃ ሊቀሙ ሞክረዋል በማለት ሰባት ተቃዋሚዎችን ገድለዋል። በሁከቱ ውስጥ ተሳትፈዋል ተብለው የተጠረጠሩ 170 ግለሰቦችን ፖሊስ በአዲስ አበባ ውስጥ ያሰረ ሲሆን ሁከቱን ለማባባስ ሞክረዋል የተባሉ ተጨማሪ 1200 ሰዎች ተይዘዋል።

## በወሲብ ዝንባሌና በጾታ ማንነት ላይ የተመሰረቱ የጥቃት የማግለልና ሌሎች የማጎሳቆል ተግባራት

በስምምነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ጾታ ወሲባዊ ተግባር ህገ ወጥ የሆነና ከሶስት እስከ 15 ዓመት እስር የሚያስቀጣ ነው። ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች (LGBTI) ላይ የሚደረግን ማግለል የሚከለክል ህግ የለም። ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች ላይ የጥቃት መፈፀምን የሚያሳዩ ሪፖርቶች ነበሩ፣ ይሁን እንጂ ብቀላን፣ ማግለልን ወይም መጠቋቆምን በመፍራት ሪፖርት የማድረግ ሁኔታ የተገደበ ነበር፡ ፡ ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ምርመራን በመደገፍ ረገድ የጥላቻ ወንጀል ህጎች ወይም ሌሎች ስለወንጀል ፍትሕ የአሰራር ዜዴዎች የሉም። ግለሰቦች በከባድ ማህበረሰባዊ መጠቋቆምና በስምምነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ፆታ ወሲባዊ ተግባር ህገ ወጥነት ምክንያት ሴት ከሴት ወሲብ ፈጻሚዎች፣ ግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ያላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ያስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ያላቸው ሰዎች በአብዛኛው ራሳቸውን አይገልጹም።የሴት ከሴት ጋር ወሲብ ፈጻሚዎች፤ የግብረሰዶማውያን፡ የባለ ሁለት ፆታ ፍናፍንቶች፤ የፆታ ቀያሪዎች እና የህብረት ፆታ ፈፃሚዎች ማህበረሰብ አቀንቃኞች/አክቲቪስቶች ክትትል እንደሚደረግባቸው ሪፖርት አድረገው ለደህንነታቸው እንደሚፈሩ ገልፀዋል። በተመሳሳይ ጾታ የወሲብ ተግባራት ውስጥ በመሳተፋቸው የታሰሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች ስለመኖራቸው የሚገልጹ ሪፖርቶች የሉም።

በአዲስ አበባ ያለው የኤይድስ ሪሶርስ (ግብዓት) ማዕከል ራሳቸውን ግብረሰዶማዊ ወይም ሴት ከሴት ጋር ወሲብ የሚፈፅሙ አድርገው የገለፁ እና አብዛኞቹ ወንዶች የሆኑ የስልክ ደዋዮች ባህርይቸውን ለውጠው መገለልን ለማስቀረት ድጋፍ መጠየቃቸውን ሪፖርት አድርጓል። አብዛኞቹ ግብረሰዶማዊያን መበርገግ ግራ መጋባት፣ የማንነት ቀውስ፣ ጭንቀት፣

ራስን ማግለል፣ ሐይማኖታዊ ግጭትና ራስን የማጥፋት ሙከራዎች እንደገጠማቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡

## ኤችአይቪ እና ኤድስ ማህበራዊ አድሎ

በኤችአይቪ/ኤድስ የተጠቁ ወይም ከበሽታው ጋር የሚኖሩ ሰዎች በትምህርት፣ በስራ ቅጥርና በማህበረሰባዊ ውህደት ረገድ የሚደርስባቸው ማህበረሰባዊ አድሎና መገለል ቀጥሏል፡፡ በኤችአይቪ/ኤድስ የተጠቁ ወይም ከበሽታው ጋር የሚኖሩ ሰዎች የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡ የችግሩን መጠን የሚገልፁ አሃዛዊ መረጃዎች (ስታቲስቲክስ) የሉም፡፡

## ሌሎች ማህበረሰባዊ ጥቃቶች ወይም ማግለሎች

በአለምአቀፍ የስደተኖች ድርጅት የመፈናቀል መከታተያ ማትሪክስ መሰረት፣ አብዛኞቹ መፈናቀሎች በጁን (በሰኔ) ወር ያጋጠሙ ሲሆን በኦሮሚያ ክፍሎች ደብብሕ በብሔሮች መካከል የተከሰተው ግጭት በደብብሕ ጌዲኦ ዞን እና በኦሮሚያ ምዕራብ ጉጂ ዞን ወደ አንድ ሚሊየን ለሚጠጉ ነዋሪዎች የነበሩባቸውን አካባቢዎች እንዲለቁ ምክንያት ሆኗል፡፡

## ክፍል 7፡ የሰራተኛ መብቶች

## ሀ. የመደራጀት ነጻነት እና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብት

ህገ መንግስቱ እና ህጉ ከመንግስት ሰራተኞችና በቀዳሚነት በመንግስት ዘርፍ ውስጥ ካሉ አንዳንድ የሰራተኞች ምድቦች በስተቀር ለሰራተኞች ማህበራትን የመመስረትና አባል የመሆን፣ ህጋዊ የስራ ማቆም እንዲሁም ሕጋዊ አድማ የማድረግና የህብረት ድርድር የማካሄድ መብትን ይሰጣል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሌሎች ድንጋጌዎችና ህጎች እነዚህን መብቶች በጣም ይገድባሉ ወይም ከመጠን ባለፈ ሁኔታ ይቆጣጠራሉ፡፡ በተለይም ህጉ የአስዳደር ሰራተኞችን፣ አስተማሪዎችን፣ የጤና እንክብካቤ ሰራተኞችን፣ ዳኞችን፣ አቃቤ ህጎችን፣ የደህንነት አግልገሎት ሰራተኞችን፣ የቤት ሰራተኞችን እና በወቅት ላይ የተመሰረተ

የግብርና ስራ የሚያካሄዱ ሰራተኞችን በማህበራት እንዳይደራጁ ይከለክላል። ህጉ የጸረ ማህበር መገለልን ቢከለክልም፣ አሰሪዎች የማህበራት አራማጆችን/አቀንቃኞችን እንዳሰናበቱ ማህበራት ሪፖርት አድርገዋል። የጸረ-ማህበር አግልሎትን በመፈፀም ጥፋተኛ የሆኑ አሰሪዎች በማህበር የስራ እንቅስቃሴዎች ምክንያት የተሰናበቱ ሰራተኞችን ወደ ስራ ገበታቸው እንዲመልሱ ህጉ የሚያስገድድ ሲሆን በአብዛኛው ይህንን አድርገዋል። የሥራ ማቆም አድማ በሚያደርጉ ላይ ብቀላ እንዳይደረግ ህጉ ቢከለክለም፣ ባለስልጣናት ግን የሥራ ማቆም አድማ በማድረጋቸው ዘጠኝ የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪዎችን አስረዋል። መንግስት አግባብነት ያላቸውን ህጎችን በተሳካ ሁኔታ አላስከበረም፣ ቅጣቶችም ጥቃቶችን ለማስቀረት በቂ አልነበሩም።

አንድ ማህበር ለመመስረት ቢያንስ 10 ሰራተኞች ያስፈልጋሉ። ሁሉም ማህበራት የመመዝገብ መብት እንዲኖራቸው ህጉ ቢደነግግም፣ መንግስት የምዝገባ መስፈርቶቹን ያላሟሉ የሰራተኞች ማህበራትን ምዝገባ ሊከለክል ይችላል። ለክልከላው በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችለው ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ የማህበር መሪ ፖለቲካዊ ያልሆነ የወንጀል ጥፋተኝነት ፍርድ ቢሆንም በዚህ መሰረት የተከለከለ ምዝገባ ስለመኖሩ ሪፖርቶች የሉም። መንግስት የአንድን ማህበር ምዝገባ በራሱ የአንድ ወገን ውሳኔ ብቻ ለመሰረዝ ይችላል። ሰራተኞች በእያንዳንዱ የስራ ቅጥር ከአንድ በላይ የሰራተኛ ማህበር አባል ለመሆን አይችሉም። የሰራተኛ ማህበር ድርጅት በገሃድ ፖለቲካዊ ሁኔታ መስራት እንደሌለበት ህጉ ይደነግጋል። የፖለቲካ ተግባር በመሳሰሉ የተከለከሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሰማራት ምክንያት የአስተዳደር ባለስልጣናት የማህበሩን ምዝገባ ለመሰረዝ በፍ/ቤት እርምጃዎች አማካኝነት እርዳት እንዲያገኙ ህጉ ይፈቅዳል።

ሰራተኞች በነጻነት እንዳይደራጁ በግልጽ ወይም ሊሆን በሚችል ሁኔታ መብቶቻቸውን የሚጥሱ ሌሎች ህጎች እና ደንቦች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህግን ያካትታል። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህጉ ምዝገባን፣ የውስጥ አስተዳደርን ማፈን እና ድርጅቶችን ማፍረስን ጨምሮ በሰራተኞች የመደራጀት መብት ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ለመንግስት ስልጣን እንደሚሰጥ የሥምምነቶችና የማሳሰቢያዎች አተገባበር አለማቀፍ የአሰሪና ሰራተኞች ድርጅት የኤክስፖርቶች ኮሚቴ አስገንዝቧል። ለምሳሌ፣ የሰራተኛ ሕብረቶች የውስጥ አስተዳደር ራስ-ገዝነታቸውን የሚቀንሱ አንዳንድ የአሰራር ደንቦችን መከተል እንዳለባቸው ህጉ ያስገድዳል። ሁለት-ሶስተኛው የማህበር አባላት የመንግስት ቁጥጥር ካለበት የኢትዮጵያ የሰራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ጋር ቁርኝት ካላቸው ድርጅቶች ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ብሔራዊ የመምህራን ማህበር ሳይመዘገብ ቀርቷል።

ህጉ ለሕብረት ድርድር መብት እውቅና ቢሰጥም፣ ይህ መብት በህጉ መሰረት በጥብቅ ተገድቧል። የጋራ ድርድር ስምምነትን ለማሻሻል ወይም ለመተካት ያለሙ ድርድሮች ጊዜው ባበቃ በሶስት ወራት ውስጥ መከናወን አለባቸው፣ አለበለዚያ በምንዳዎች እና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች ላይ የበፊቶቹ ድንጋጌዎች መተግበራቸው ያቆማል። የድርጅት ማህበራት በፋብሪካ/ኢንዱስትሪ ደረጃ ብቻ በምንዳ ክፍያ ላይ እንዳይደራደሩ ያግዳል። የመንግስት ት/ቤት አስተማሪዎችን ጨምሮ የመንግስት ሰራተኞች በተቀጣሪ ሰራተኞች የተቋቋሙ የሙያ ማህበራትን የመመረስትና አባል የመሆን መብት ቢኖራቸውም የሕብረት ድርድር ማድረግ አይችሉም። በመንግስት ዘርፍ ውስጥ የግልግል (አርቢትሬሽን) የአሰራር ሥራቶች ከግሉ ዘርፍ ይልቅ የበለጠ አጋጅ ናቸው። ሕጉ የሰራተኞች ወይም የአሰሪዎችን ድርጅቶች በመመስረት፣ በማካሄድ ወይም በማስተዳደር ረገድ በሌሎች አካላት በሚደረጉ የጣልቃ ገብነት ተግባራት ላይ ፍቱንና በቂ ቅጣቶች አይደነገግም። በመደበኛው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ ያሉ ማህበራት የአሰሪና ሰራተኛ ደንቦችን ለማስከበር አንዳንድ ጥረቶችን አድርገዋል።

ሰራተኞች ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ ህገ መንግስቱና ህጉ ቢደነግጉም ህጋዊ ስራ የማቆም አድማ ተግባራትን በሚያግድ መልኩ አስቸጋሪ የሚያደርጉ በጣም ውስብስብና ጊዜ የሚፈጁ ፎርማሊቲዎችን የሚያዙ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይይዛል። ተበዳይ ሰራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በፊት ከአሰሪዎች ጋር ለመታረቅ እንዲሞክሩ ህጉ የሚያዝ ሲሆን ረዥም  የክርክር እልባት መስጫ ሂደትን ያካትታል። እነዚህ ድንጋጌዎች አሰሪዎች ሰራተኞችን ወደ መስሪያ ቤት እንዳያስገቡ ባላቸው መብት ላይም በእኩል ደረጃ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ፈቃድ ላለው የስራ ማቆም አድማ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ሁለት ሶስተኛው እንዲህ አይነቱን እርምጃ መደገፍ አለባቸው። ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ወይም ወደ አሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቶች ቦርድ ካልተመራ፣ ማህበሩ ወደ እነዚህ ሁለት አማራጮች መሄድ ሳያስፈልገው የስራ ማቆም አድማ የማድረግ መብትን ይይዛል፣ ይህ የሚሆነው ግን ለሌላው ወገን እና ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢያንስ የ10 ቀናት ማስታወቂያ ከሰጡና በእርቅ ጉዳይ ላይ ጥረቶች ካደረጉ ነው።

በተጨማሪም ህጉ የአየር ትራንስፖርትና የአውቶብስ አገልግሎቶችን፣ የኤሌክትሪክ ሐይል አቅራቢዎችን የነዳጅ ማደያ ሰራተኞችን የሆስፒታልና ፋርማሲ ሰራተኞችን፣ የእሳት አደጋ ተከላካዮችን፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ሰራተኞችንና የከተማ ውስጥ የጽዳት ሰራተኞችን ጨምሮ መሰረታዊ አገልግሎቶች በሚሰጡ ሰራተኞች የሚደረጉ የስራ ማቆም አድማዎችን ያግዳል። የመሰረታዊ አገልግሎቶች ዝርዝር የዓለምአቀፍ ሰራተኞች ድርጅት (ILO) ስለ መሰረታዊ አገልግሎቶች ከሰጠው ፍቺ አልፎ የሚሄድ ነው። በአድመኞች ላይ ብቀላ እንዳይደረግ ህጉ ቢከለክልም ያልተፈቀዱ የስራ ማቆም እርምጃዎች በማካሄዳቸው ጥፋተኛ በሆኑ ማህበራትና

ሰራተኞች ላይ የፍትሐብሔርና የወንጀል መቀጫዎችን ጭምር ይደነግጋል። ይህንን ደንብ መጣስ የሚያስቀጣ ሲሆን በማህበር ከተፈፀመ ከ1200 ብር (43 ዶላር) ባልበለጠ መቀጫ ወይም በግለሰብ ሰራተኛ ከተፈፀመ ከ300 ብር (11 ዶላር) ባልበለጠ መቀጫ ያስቀጣል። የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ድንጋጌዎች ተጨማሪ ክብደት ያላቸው መቀጫዎችን የሚያዝ ከሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ የተተረጎመው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል። መንግስትን፣ ህዝብን ወይም የግል ጥቅሞችን በሚጎዳ ሁኔታ የሥራ ማቆም አድማ የሚያደርግ፣ ሌሎችን አድማ እንዲያደርጉ የሚገፋፋ ወይም ስራውን/ዋን በትክክለኛ ሁኔታ የማያከናውን ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የጉልበት ስራን የመስራት ግዴታ ለሚያካትት እስር ተገዢ ይሆናል።

የቤት ሰራተኞችንና በወቅት ላይ የተመሰረተ የግብርና ስራ የሚሰሩ ሰራተኞችን ጨምሮ መደበኛ ያልሆነ የጉልበት ስራ ዘርፍ በማህበር አይደራጅም ወይም በአሰሪና ሰራተኛ ህጎች ከለላ አይሰጠውም። ህጉ ሰራተኞችን በስራ ቅጥር ግንኙነት ውስጥ እንዳሉ ሰዎች ይተረጉማቸዋል። የሠራተኞች በበቂ ሁኔታ አለመኖር መንግስትን በህግ ከለላ ላገኙ ዘርፎች ተፈጻሚ ህጎችን በስኬት ከማስከበር አግዶታል። የፍ/ቤት የአሰራር ሥርዓቶች ብዙውን ጊዜ ለተራዘሙ መዘግየቶችና ይግባኞች ተገዢ እየሆነ ነው። ከፍተኛ የሥራ አጥነት፣ የብቀላ ፍራሐት እና የአሰሪና ሰራተኛ ክሶችን ችሎት በመስማት ያሉት ረጃጅም መዘግየቶች ሰራተኞችን በስራ ማቆም አድማዎች ወይም በሌሎች የሰራተኛ እርምጃዎች ከመሳተፍ እንዳገዳቸው የአሰሪና ሰራተኛ ሃላፊዎች ሪፖርት አድርገዋል። መንግስት አደራጆችን ወይም የሰራተኛ መሪዎችን ለመቅጣት የጸረ ሽብርተኛን ህግ መጠቀሙን የዓለምአቀፍ አሰሪና ሰራተኞች ድርጅት ይተቻል።

ብዙ ጊዜ ሪፖርት ባይደረግም የፀረ-ማህበር እንቅስቃሴዎች ተከስተዋል። ሰራተኞች ማህበራትን እንዳይመሰርቱ አንዳንድ ትልልቅ የውጭ ኢንቨስተሮች በአብዛኛው አለመፍቀዳቸውን፣ የማህበር መሪዎችን ዘወትር ማዘዋወራቸውን ወይም ማሰናበታቸውን እና አባላት ማህበራትን ትተው እንዲወጡ ማስፈራራታቸውን እና ጫና መፍጠራቸውን የዘገቡ የሚዲያ ሪፖርቶች ነበሩ። በፍ/ቤቶች ውስጥ ባሉ የክስ ውዝፎች ምክንያት ህገ ወጥ የተባሉ የሥንብት ክሶችን ለመወሰን ብዙ ጊዜ ዓመታት ይወስዳሉ።

## ለ. አስገዳጅ ወይም የግዴታ የጉልበት ስራ ክልከላ

ህጉ ሁሉንም ዓይነት የግዴታ ወይም አስገዳጅ የጉልበት ስራን የሚከለክልና በወንጀል የሚያስጠይቅ ቢሆንም ፍ/ቤቶች የቅጣት እርምጃ በማድረግ አስገዳጅ የጉልበት ስራ እንዲያዙ

ይፈቅድላቸዋል፡፡የባርነት የጥፋተኝነት ፍርድ ከ5 እስከ 20 ዓመት እስርና መቀጫ ያስፈርዳል፡፡ መንግስት በተሳካ ሁኔታ ህጉን ያላስከበረ በመሆኑ አስገዳጅ የጉልበት ስራ ተከስቷል፡፡

የፌዴራል መንግስት በ2015 (2007/2008) በፀረ ህገ-ወጥ ዝውውር የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ላይ አጠቃላይ የጥገና ለውጥ በስራ ላይ አውሏል፡፡ ባርነትን፣ በእዳ ምክንያት አገልጋይ አድርጎ መያዝን፣ በግዴታ በሴተኛ አዳሪነት ማሰማራትን እና በገባርነት መጨቆንን ጨምሮ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርንና ብዝበዛን በሚያካሄዱ ላይ ህጉ እስከ እድሜ ልክ እስር እና 500,000 ብር (17,900 ዶላር) የሚደርስ ከባድ ቅጣት ያዝዛል፡፡ መቀጫዎቹ በተለይ በጥቃት ላይ እየጨመረ ከሚሄደው የህግ ማስከበር ትኩረት ጋር ሲጣመሩ ድርጊቱን ለማገድ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በፌዴራልና በክልል ደረጃዎች ለሚገኙ ፖሊሶች በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና በብዝበዛ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡

ወደ ባህረ ሰላጤው ሐገራት በጉልበት ስራ ስደት ላይ የተደረገው ክልከላ ፀንቶ የቆየ ቢሆንም መንግስት ከአብዛኞቹ የባህረ ሰላጤው ሐገራት ጋር የሁለትዮሽ የስራ ስምምነቶች አድርጓል፡፡

ብዙውን ጊዜ በአስገዳጅ ድርጊት ስር ያሉ አዋቂዎችና ልጆች በጎዳና ላይ ንግድ፣ በልመና፣ በእጅ በሚሸመኑ ጨርቆች በባህላዊ የሽመና ስራ ወይም በግብርና ስራ ላይ ተሰማርተዋል፡፡ እንዲሁም ልጆች በአስገዳጅ የቤት ውስጥ የጉልበት ስራ ይሰራሉ፡፡ በእዳ ምክንያት በገባርነት የመያዝ ሁኔታዎች በይበልጥ በገጠር አካባቢዎች ውስጥ በባህላዊ ሽመና፣ በሸክላ ስራ፣ በከብት እረኝነት እና በሌሎች የግብርና ስራዎች ውስጥም ተከስተዋል፡፡

መንግስት አንዳንድ ጊዜ እስረኞችን ከማረሚያ ቤቶች ውጭ ለግል ድርጅቶች እንዲሰሩ የሚያሰማራ ሲሆን፣ ይህንን ድርጊት የአለምአቀፍ አሰሪና ሰራተኛ ድርጅት እንደ አስገዳጅ የጉልበት ስራ መውሰድ ይቻላል ብሏል፡፡

በ *WWW.state.gov/j/tip/rls/tiprpt/.* ላይ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የሰዎችን ህገ-ወጥ ዝውውር ሪፖርት ጭምር ይመልከቱ፡፡

## ሐ. የሕፃናት የጉልበት ስራ ክልከላ እና አነስተኛው የሥራ ቅጥር እድሜ

ህጉ በጣም አስከፊ የሆኑ  ማንኛቸውንም አይነት የሕፃን ልጅ የጉልበት ሥራ ይከለክላል፡፡ መንግስት አግባብነት ያላቸውን ህጎች በተሳካ ሁኔታ ያልተገበረ ሲሆን፣ መቀጫዎችም የህግ ጥሰቶችን ለማገድ በቂ አይደሉም፡፡

በህጉ መሰረት ለቀን ክፍያ ወይም ለደመወዝተኝነት አነስተኛ የስራ ቅጥር እድሜ 14 ዓመት ነው። አነስተኛ የእድሜ ድንጋጌዎች ግን በውለታ/በኮንትራት ለሚሰሩ ሰራተኞች ብቻ እንጂ እጅግ ብዙ የስራ ቅጥር ህፃናትን በሚያካትተው ለራሳቸው በተቀጠሩ ወይም የማይከፈልበት ስራ በሚሰሩ ልጆች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም። እድሜያቸው ከ14 እስከ 18 የሆኑ ህጻናት አደገኛ ወይም የሌሊት ስራ እንዳይሰሩ ህጉ ይከለክላል። የህጻን ልጅን ጤንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ማንኛውም ስራ አደገኛ ስራ ሆኖ በህግ ይተረጎማል። የተከለከሉ የሥራ ዘርፎች የመንገደኛ ማጓጓዣ ትራንስፖርትን፣ በኤሌክትሪክ ሐይል ማመንጫ ኢንዱስትሪዎች መስራትን፣ የፋብሪካ ስራን ከመሬት ወለል በታች መስራትን፣ ጎዳና ማጽዳትን እና ሌሎች ብዙ ዘርፎችን ያካትታሉ። በአደገኛ ስራ ላይ ከተደረገው ክልከላ በመነሳት እድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በሙያ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዳይማሩ ህጉ በግልጽ ያግዳቸዋል። ከ14 እስከ 18 እድሜ ያላቸው ልጆች በቀን ከሰባት ሰዓታት በላይ፣ ከምሽቱ 4፡00 እስከ ጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ወይም በበዓል ቀናት ወይም በእረፍት ቀናት እንዲሰሩ ህጉ አይፈቅድም።

የሕጻናት የጉልበት ስራ ከባድ ችግር ሆኖ ዘልቋል። (በተጨማሪ ክፍል 7.ለ ይመልከቱ)፣እናም በርካታ ቁጥር ያላቸው ህጻናት በተከለከሉ፣ አደገኛ በሆኑ በተለይ በግንባታው ዘርፍ ይሰራሉ፡ ፡

የትምህርት ቤት የተማሪዎች ምዝገባ በተለይ በገጠር አካባቢዎች ዝቅተኛ ነው። ትምህርት የመማርን አስፈላጊነት ለማጠናከር፣ ልጆች በዋናነት በግብርና ስራ በተሰማሩባቸው ማህበረሰቦች ላይ መያድ፣ መንግስታዊ እና ማህበረሰብ-አቀፍ የጋራ ግንዛቤ ማስጨበጫ ጥረቶች ትኩረት አድርገዋል። መንግስት በግብርናው ዘርፎች ውስጥ የሕጻን ልጅ የጉልበት ስራ ችግርን ለመዋጋት የግብርና አሰራሮችን በማዘመንና ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ላይ መዋዕለ-ንዋይ አፍስሷል።

ልጆች በገጠርም በከተማ አካባቢዎችም ብዙ ጊዜ በለጋ እድሜያቸው መስራት ይጀምራሉ። በተለይ ሕይወትን በማቆያ የግብርና ምርት ስራ፣ በባህላዊ ሽመና፣ በአሳ ማጥመድ እና በቤት ውስጥ ስራ የህጻን ልጅ የጉልበት ስራ ተስፋፍቶ ይገኛል። ቁጥራቸው እያደገ የመጣው ልጆች በግንባታ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። በገጠር አካባቢዎች ያሉ ህጻናት በተለይም ወንድ ልጆች ከብት በማገድ፣ ጥቃቅን እቃዎችን በመሸጥ፣ በማጨድና አረም መንቀልን በመሳሰሉ ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉ ሲሆን ሴቶች ልጆች ደግሞ ማገዶ በመሰብሰብና ውሃ በመቅዳት ላይ ተሰማርተዋል። ትንንሽ ልጆች ወርቅ የማምረት ስራ ይሰራሉ። በአነስተኛ ደረጃ በሚካሄድ የወርቅ ማዕድን ስራ የማዕድን ጉድጓዶችን ይቆፍራሉ እንዲሁም ከባድ የውሃ ጭነቶችን

ይሸከማሉ፡ ወላጅ አልባ ልጆችን ጨምሮ በከተማ አካባቢዎች ያሉ ህጻናት አብዛኛዎቹ ብዙውን ጊዜ ለረጅም ሰዓታት የቤት ውስጥ አገልግሎት ስለሚሰጡ ትምህርታቸውን አዘውትረው እንዳይከታተሉ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም ልጆች በማምረቻ ቦታዎች፣ ጫማ በመጥረግ፣ ልብስ በመስፋት፣ መኪና በመጠበቅ፣ በህዝብ ትራንስፖርት፣ በጥቃቅን ንግድ፣ በተሸካሚነት እና የታክሲ ተራ በማስያዝ ይሰራሉ። አንዳንድ ልጆች በአነስተኛ ክፍያ ወይም ምንም ሳይከፈላቸው እና የስራ ላይ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች ሳይኖራቸው በአደገኛ ከባቢ-ሁኔታዎች ውስጥ ለረጅም ሰዓታት ይሰራሉ። ህጻናት የጉልበት ሰራተኞች አካላዊ፣ ወሲባዊ እና ስሜታዊ ጥቃትን የመሳሰሉ በደሎች በአሰሪዎቻቸው ይደርስባቸዋል።

ህገ-ወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች ድህነት ከተንሰራፋባቸው የገጠር አካባቢዎች ልጃገረዶችን በመበዝበዝ በዋናነት በቤት ውስጥ የባርነት አገልግሎት እና በሐገሪቱ የወሲብ ንግድ ውስጥ ያሰማሯቸዋል።
በWWW.dol.gov/ilab/reports/child-labor/findings/ ላይ በጣም በከፉ የህጻን ልጅ ጉልበት ብዝበዛዎች ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የጉልበት ስራ ግኝቶችን ጭምር ይመልከቱ።

## መ. ከቅጥር እና ከሥራ ጋር የተያያዘ ማግለል

ህጉ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣በትዳር ሁኔታ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ ትስስር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በእርግዝና፣ በማህበረ ኢኮኖሚ ደረጃ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ ወይም በ “ማናቸውም ሌሎች ሁኔታዎች” ላይ ተመስርቶ የሚደረግ ማግለልን ይከለክሏል። ቅጥርንና የሥራ አይነትን አስመልክቶ ህጉ ማግለልን ይከለክላል፣ ይሁን እንጂ ባለስልጣናት እነዚህን መብቶች ባልተመጣጠነ ሁኔታ በስራ ላይ ያውላሉ። ህጉ በእርጉዝ ሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ ላለ ተጨማሪ ጫና በልዩ ሁኔታ እውቅና ይሰጣል። ከላይ በሰፈሩት ማናቸውም ምክንያቶች ላይ ለሚደረግ ማግለል የጥፋተኝነት መቀጫው 1200 ብር (43 ዶላር) ነው። መንግስት ህጉን ለማስከበር የተገደቡ እርምጃዎችን ነው የወሰደው። የወሲብ ዝንባሌ፣ የጾታ ማንነት እና የኤችአይቪ ተሸካሚ መሆን በህጉ መሰረት ከለላ ለማግኘት መሰረት የላቸውም፡
፡

በቅጥርና በሥራ ዓይነት ከወንዶች ይልቅ አነስተኛ የቅጥር እድል ባላቸው ሴቶች ላይ መገለል የሚያጋጥም ሲሆን፣ ስራዎች ቢገኙም ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ አይፈፀምም። በቅጥርና በሥራ ዓይነት ውስጥ የማግለል ሁኔታ በወሲብ ዝንባሌ እና/ወይም በፆታ ማንነት ላይ ይከሰታሉ።

በስደተኛ ሰራተኞችም ላይ የማግለል ተግባራት ተከስተዋል።

## ሰ. ቅቡልነት ያላቸው የስራ ሁኔታዎች

በብሔራዊ ደረጃ የተቀመጠ አነስተኛ የክፍያ ተመን የለም። አንዳንድ የመንግስት ተቋማት እና የመንግስት ድርጅቶች የራሳቸውን አነስተኛ ክፍያዎች ይወስናሉ። በቁጥር ከፍተኛ የደመወዝ ተከፋይ ቡድን የሆኑት የመንግስት ዘርፍ ሰራተኞች በወር አነስተኛ ወደ 615 ብር (22 ዶላር) ገደማ ያገኛሉ። ለድህነት ገቢ ደረጃ ኦፊሴላዊው ግምት በወር 315 ብር (11 ዶላር) ነበር። በአጠቃላይ መንግስት የክፍያ ህጎችን በስኬት ስራ ላይ አላዋለም።

ህጉ ከ24 ሰዓት የእረፍት ጊዜ ጋር ቢበዛ የ48-ሰዓት ህጋዊ የስራ ሳምንት፣ ለትርፍ ጊዜ ስራ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈል፣ እና በግዴታ የሚሰራ ተጨማሪ የትርፍ ጊዜ ስራ እንዳይኖር ይደነግጋል። አሰሪዎች የትርፍ ሰዓት ስራን ለመጠቀም የሚችሉባቸው 4 ሁኔታዎች አሉ። እነርሱም፡- የስራው አስቸኳይነት፣ አደጋ፣ የሰራተኛ መቅረት፣ እና የአማራጮች እጦት ናቸው። በተጨማሪም አሰሪዎች በቀን ከሁለት ሰዓታት፣ በወር ከ20 ሰዓታት እና በዓመት ከ100 ሰዓታት ለሚበልጥ ጊዜ ሰራተኞቻቸውን የትርፍ ሰዓት ስራ ማሰራት የለባቸውም። አገሪቱ በዓመት 13 ክፍያ የሚፈፀምባቸው የህዝብ በዓላት አሏት። ህጉ በመንግስት ድርጅቶች እና በመንግስት የፋይናንስ ተቋማት የሚሰሩ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲያገኙ መብት ይሰጣቸዋል፤ የመንግስት ሰራተኞች ለትርፍ ሰዓት ስራ ማካካሻ የሚሆን የእረፍት ጊዜ ይሰጣቸዋል።

መንግስት፣ ኢንዱስትሪዎች እና ማህበራት በብዙ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለሰራተኛ ደህንነት ሙሉ መፍትሔ በማይሰጡ የስራ ላይ ደህንነትና የጤና ስታንዳርዶች ላይ ይደራደራሉ። የቤት ሰራተኞችን እና በወቅት ላይ የተመሰረተ የግብርና ሰራተኞችን ጨምሮ የሰራተኞች ማህበር ከመመስረት በልዩ ሁኔታ ይከለክላሉ፤ እናም  በአጠቃላይ በስራ ቦታ ውስጥ ከጤና እና ከደህንነት ጥበቃ ደንቦች ጥቅም አያገኙም።

የአሰሪና ሰራተኞች ሚኒስቴር የኢንስፔክሽን መምሪያ የስራ ቦታ ስታንዳርዶችን የማስከበር ሃላፊነት ነበረበት። የሥራ ላይ ደህንነት እና የጤና እርምጃዎች በተዋጣ ሁኔታ ስራ ላይ አልዋሉም። ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደንብ መከበርን ለመከታተል ቋሚ የሰራተኛ ፍተሻዎች ቢያደርግም፣ መንግስት ያለማቀፉ የሰራተኞች ድርጅት ካሳሰበው 1321 ከግማሽ የሚያንሱ 516 የሰራተኛ ተቆጣጣሪዎችን/መርማሪዎችን ብቻ ነው የቀጠረው። የሚኒስቴር መ/ቤቱ በጣም የተገደበ አስተዳደራዊ አቅም፣ ተፈጸሙ የተባሉ የመብት ጥሰት ውንጀላዎችን

ለመቀበል፣ ለመመርመርና ለመከታተል የሚሆን ውጤታማ የአሰራር ዘዴ ማነስ፣ እና ዝርዝር መረጃ የያዙ ዘርፍ-ተኮር የጤናና የደህንነት መመሪያዎች እጥረት የእነዚህ ስታንዳርዶች ስኬታማ ትግበራትን አደናቅፏል፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ እጅግ በቅርብ የበጀት ዓመት ውስጥ 46,000 ምርመራዎችን ያጠናቀቀ ሲሆን፣ አስተማማኝነት የሌላቸውን ሁኔታዎች ለይቶ የማወቁ ሃላፊነት በሰራተኛ ተቆጣጣሪዎች/መርመሪዎች ላይ ማረፉ በአብዛኛው ግልጽ ነው፡፡

በክፍያ-የሰራተኛ ቅጥር እድል ያገኘው በከተሞች አካባቢ የተከማቸው የህዝቡ አነስተኛ መቶኛ መጠን የሆነው ብቻ ነው፡፡ መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ ውስጥ የሚፈፀሙ ክፍያዎች በአብዛኛው ሕይወትን ከማቆያ ደረጃዎች በታች ናቸው፡፡

በወቅት ላይ የተመሰረቱ የግብርና ሰራተኞች የካሳ ክፍያ፣ ጥቅማጥቅሞች እና የሥራ ሁኔታዎች በማህበር  ከታቀፉ ቋሚ የግብርና ተቀጣሪ ሰራተኞች እጅግ ያነሱ ናቸው፡፡ መንግስት ህጉን ለማስከበር የሰራው አነስተኛ ነው፡፡ በመደበኛው ዘርፍ አብዛኞቹ ሰራተኞች በሳምንት 39 ሰዓታት ነው የሚሰሩት፡፡ ብዙዎቹ የውጭ ሐገር፣ የሥደተኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የጉልበት ሰራተኞች በሳምንት ከ48 ሰዓታት በላይ ይሰራሉ፡፡
የሐገሪቱ ኢኮኖሚ ዋነኛ መሰረት በሆነው የግብርና ዘርፍ ውስጥ አደገኛ የስራ ሁኔታዎች አሉ፡ ፡ ስለ ሞት እና ጉዳቶች የሚገልፁ መረጃዎች ባይገኙም በግንባታና በኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ አደገኛ እና በዝባዥ የሥራ ሁኔታዎች እንዳሉ የሚገልፁ ሪፖርቶችም አሉ፡፡